haughty ትዕቢተኛ (words) የትዕቢት

haul (pull) ጎተተ (transport) አጓጓዘ

haunch ወገብ

haunt (inhabit) ኖረ (በት) ; (trouble) አስበረገገ ፤ አሸበረ (visit persistently) አዘወተረ

have አለ -with object suffix pronouns

haven ወደብ ; (for fugitives) መሸሸጊያ

havoc ጥፋት

play havoc with አበላሸ

hawk ጭልፊት

hay ድርቆሽ፡

haywire, be --- ትርምስምስ፡ አለ

go haywire መስ፡ ቅጡ፡ ጠፋ.

hazard (n.) አደጋ

hazardous አደገኛ

haze ጭጋግ

hazy ጭጋጋም፡ ; (of ideas) ግልጽ፡ ያልሆነ

he እርሱ ፤ እሱ፡

head (vt.) መራ ; (a department) ሹም፡ ሆነ ፤ ኃላፊ፡ ሆነ፡

head, vi. (move toward) አመራ፡

head (n.) ራስ፡ ; (of a nail) ጭንቅላት፡ ; (of family) አውራ ; (of government) መሪ ; (of a firm) ኃላፊ ; (of a gang) አለቃ ; (of a river) ምንጭ ; (of lettuce) ጥቅል

heads or tails ዘውድ፡ ወይስ፡ አንበሳ

be head and shoulders above በለጠ

come to a head (quarrel) ~~[illegible]~~ ተካረረ ; (struggle for power) ተፋፋመ

lose one's head ናላው፡ ዞረ፡

make head or tail ተረዳ(ው) ፤ ገባ(ው)

head (adj.) ዋና

headache የራስ፡ ምታት

headdress የጸጉር፡ አሠራር፡

heading ርእስ፡

headlight የፊት፡ መብራት፡

headline አርእስተ፡ ዜና፡

headman ~~ዲሬክተር~~፡ ጭቃ፡ ሹም

headmaster ዲሬክተር፡

headquarters (of army) ጠቅላይ፡ መምሪያ፡

(of an office) ዋና፡ መሥሪያ፡ ቤት፡

headrest ትራስ፡

headstall ልጓም፡

headstrong ሐሳበ፡ ግትር፡

headwaters ምንጭ፡

heal (vt.) አዳነ፡

heal (vi.) ዳነ፤ ጠገገ፡

healer መድኃኒተኛ፡

health ጤንነት

Ministry of Health የጤና፡ ጥበቃ፡ ሚኒስቴር፡

healthy (person) ጤናማ፡

(body) ጤነኛ፡ ; (climate) ለጤና፡ የሚስማማ፡

heap (v.) ቈለለ፡

heap up አከማቸ

heap (n.) ክምር፤ ቁልል

heaps of ብዙ፡

hear ሰማ ; (of a judge) አየ;

(accept) ተቀበለ

hearing መስማት ; (ability to hear) የመስማት፡ ችሎታ፡

give a hearing ክርክር፡ አዳመጠ፡

hearsay አሉባልታ፡

hearse የሬሳ፡ መኪና

heart ልብ ; (innermost part) ውስጥ ; (center) መካከል

(enthusiasm) መንፈስ ; (vital part) ዋና፡ ነገር

by heart በቃል

have a heart ርኅራኅ፡ ነው

lose heart ተስፋ፡ ቆረጠ

take heart ተጽናና

take heart! አይዞህ

heart attack የልብ፡ ድካም፡

heartbeat የልብ፡ ትርታ

heartburn ቃር

hearten አበረታታ

hearth ምድጃ፡

heartily ከልብ

heartless ግፈኛ

heartsick, be --- በጣም፡ አዘነ፡

hearty (welcome) ከልብ፡ የመነጨ;

(meal) አጥጋቢ

heat (v.) አሞቀ፡

heat (n.) ሙቀት ; (of the sun) የፀሐይ፡ ሐሩር

heated (adj.) የጋለ፤ የተፋፋመ

heathen አረመኔያዊ

heave, vt. (lift with effort) በስንት፡ ችግር፡ አወጣ

(hurl) በችግር፡ ወረወረ

heave, vi. (bulge) ጉብ፡ አለ

(rise and fall repeatedly) ከፍ፡ ዝቅ፡ አለ

heaven መንግሥተ፡ ሰማያት

heavens ሰማይ፡

heavens! አቤት፡ አቤት

for heavens sake ስለ፡ እግዚአብሔር፡ ብለህ

heavenly የሰማይ ; (day) ብሩህ ; (spot) በጣም፡ አስደሳች

heavily በኀይል

heavy ከባድ ; (expenses) ከፍ፡ ያለ; (cloth) ወፍራም ; (sleep) ድብን፡ ያለ ; (smoke) ጥቅጥቅ፡ ያለ ; (drinker) ንፍስኛ

heavy artillery ከባድ፡ መሣሪያ

Hebrew ዕብራይስጥ

hectic የግርግር

hedge (vt.) አጠረ

hedge, vi. (avoid being frank) አድበሰበሰ፡ አለፈ

hedge (n.) የተክል፡ አጥር ፤ የቁጥቋጦ፡ አጥር

heed (v.) ተቀበለ ፤ ሰማ

heed (n.) take --- (pay attention ሰማ; (be careful) ተጠነቀቀ

heedful, be --- በጥንቃቄ፡ ተመለከተ፡

heedless የማይጠብቅ፡

heel (v.) ተረከዘ፡ አገገ፡

heel (n.) ተረከዝ

hefty (person) ጡንቻኛ፡ ; (book) በጣም፡ ትልቅ፡

heifer ጊደር

height ርዝመት ; (of mountain) ከፍታ ; (of man) ቁመት

heighten (a fence) አስረዘመ; (anger) አባሰ ; (the value) አስወደደ፡

heinous አስቃቂ፡

heir ወራሽ፡

heir apparent አልጋ፡ ወራሽ፡

heirloom ቅርስ፡

hell ጀሀነም፡

helmet የራስ፡ ቁር ፤ የራስ፡ ባርኔጣ፡

help (v.) ረዳ ; (of medicine) አሻለ

help oneself (to food) ተጋበዘ

help out ረዳ፡

help (n.) እርዳታ፡ ; (helpers) ረዳቶች፡

helper ረዳት፡

helpful ለመርዳት፡ ዝግጁ፡

be helpful ረዳ፡

helpless (civilian) መከላከያ፡ የሌለው

be helpless ደከመ፡ ; (have no power) ሥልጣን፡ የለውም፡

hem (v.) ቀመቀመ፡

hem (n.) ቅምቅማት ፤ ጠርዝ፡

hemisphere ንፍስ፡ ዓለም፡

hemorrhage የብዙ፡ ደም፡ መፍሰስ፡

hemorrhoids የአህያ፡ ኪንታሮት፡

hen ዶሮ፡

hence ከ... በኋላ፡

henceforth ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡

her እሷን፣ or object suffix pronouns

herald (v.) አበሰረ፡

herald (n.) ዐዋጅ ፤ ነጋሪ

herb ዕፅ

herbs ቅጠላ፡ ቅጠል፡

herbivorous ዕፅ፡ በል፡

herd (v.) አጎረ፡

herd (n.) መንጋ፡

herdsman እረኛ፡

here እዚህ፡

here and now አሁኑኑ፡

here and there አልፎ፡ አልፎ፡

hereabouts እዚህ፡ ገደማ፡

hereafter ከእንግዲህ፡

the hereafter ወዲያኛው፡ ዓለም፡

hereditary ሊወርስ፡ ሊቀረስ፡ የመጣ፡

be hereditary በዘር፡ ተላለፈ፡

heredity ዘር

herein (in this place) እዚህ፡ ውስጥ

(in this matter) እዚህ፡ ላይ፡

heresy መናፍቅነት፡

heretic መናፍቅ፡

heretofore እስካሁን፡ ድረስ

hereupon በዚህም፡ ጊዜ፡

heritage ቅርስ፡

hermit ባሕታዊ፡

hernia ቡቃ ፤ ቡአ

hero ጀግና ፤ ባለጀብዱ፡

(leading character in a story) ባለ፡ ታሪክ፡

heroic (deed) ጀግንነት ፤ የጀብዱ፡

(person) ጀግና፡ ; (measures) የድፍረት፡

heroism የጀግንነት፡ ሙያ፡

hers የርሷ ፤ የሷ፡

herself, she --- ራሷ ፤ እርሷ፡ ራሷ

be herself እንደ ወትሮዋ፡ ናት፡

by herself ራሷ.

hesitant (person) ወላዋይ፡

(speech) እየመነታ፡ የሚያደርገው፡

hesitate አመነታ፡

hesitation ማመንታት፡

heterogenous ቅይጥ፡

hew (stones) ጠረበ ; (logs) ቆረጠ

hiatus ክፍተት፡ ቦታ፡

hiccups ስርቅታ

hidden የተሰወረ.

hide (vt.) ደበቀ ፤ ሰወረ ፤ ሸሸገ፡

hide (vi.) ተደበቀ ፤ ተሸሸገ

hide (n.) ቆዳ

hide-and-seek ድብብቆሽ

hide-away መደበቂያ

hideous (crime) አስቃቂ፡

(face) አስከፊ፡

hideout መደበቂያ ፤ ጎሬ፡

hiding, go into --- ተደበቀ

hierarchy ባለ፡ሥልጣናት

high ረጅም፡ ; (office) ከፍተኛ፡ ;
 (opinion) ከፍ፡ያለ ; (fever)
 ኃይለኛ ; (voice) ቀጭን ;
 (price) ውድ፡

highborn ከታላቅ፡ የተወለደ፡

highbrow የተማረ

highanded, --- treatment መጨቆን፡

highland ደጋ

highly በጣም ; (with approval)
 በአድናቆት

Highness ልዑል

high-pitched ቀጭን

high priest ሊቀ፡ካህናት

high ranking ከፍተኛ፡

high school ሁለተኛ፡ደረጃ፡ትምህርት፡ ቤት፡

high spirits, be in --- ደስ፡
 ደስ፡አለ(ው)

high strung ድንጉጥ

highway አውራ፡ጎዳና

hijack ጠለፈ

hijacking የአውሮፕላን፡መጠለፍ፡

hike (v.) ተጓዘ

hike (n.) ሽርሽር፡

hilarious የሚያስቅ፡

hill ኮረብታ፡

 down the hill ቁልቁለቱን፡

hillock ጉብታ፡

hillside የኮረብታ፡ጎን፤ የተራራ፡ጥግ

hilltop የኮረብታ፡ጫፍ፤ አፋፍ፡

hilly ኮረብታማ፡

him እሱን, or object suffix
 pronouns

himself ራሱ

 be himself እንደ፡ወትሮው፡ነው

 by himself ብቻውን፡

hind የኋላ

hinder አደናቀፈ፤ ዕንቅፋት፡ሆነ፡

hinderance ዕንቅፋት

hinge (v.), --- on ተመሠረተ

hinge (n.) ማጠፊያ

hint (v.) አመለከተ፤ አስገነዘበ

hint, n. (advice) ምክር ;
 (suggestion) ጥቆማ

 give a hint አስታወቀ፤ ጠቆመ

hip ወገብ፡

hippopotamus ጉማሬ

hire, v. (a servant) ቀጠረ;
 (a house) ተከራየ

his የሱ, ው possessive suffix
 pronouns

hiss አፏጨ ; (air) ቱሽ፡አለ

historian ታሪክ፡ጸሐፊ

historic ታሪካዊ

historical (event) ታሪካዊ
 (costume) የጥንት

history ታሪክ

hit መታ ; (ball) ለጋ ;
(crush against something) ከ... ጋር፡ ተጋጨ ; (have a painful effect on) አስደነገጠ

hit against ገጨ

hitch (v.) አሰረ፡

hitch (n.) መሰናክል

hither ወዲህ

hitherto እስካሁን፡ ድረስ

hive ቀፎ

hoard (v.) አከማቸ

hoar-frost አመዳይ

hoarse ጎርናና

hoax ፈጠራ

hobble ሰነከለ

hobble along እየተወተረተረ፡ ሄደ

hobby የትርፍ፡ ጊዜ፡ ማሳለፊያ

hock ቋንጃ

hockey ገና

hoe (v.) ኰተኰተ

hoe (n.) ዶማ

hog አሳማ

hoist (v.) ሰቀለ

hold (vt.) ያዘ ; (control) ገታ ; (believe) አመነ ; (breath) ቁፓ አደረገ ; (a meeting) አደረገ

hold, vi. (endure) ቆየ ; (of a rule) ሠራ ; (of a dike) አልተበገረም (of a knot) አልተፈታም

hold back አስቀረ; (evidence) ሸሸገ

hold off ዘሎ፡ ፋን፡ ብሎ፡ ዘገየ

hold out (a hand) ዘረጋ

hold up (head) ቀና፡ አደረገ ;
(the trousers) ታጠቀ
(with gun) አስፈራርቶ፡ ቀማ

hold (n.) አያያዝ ; (influence) ተጽዕኖ

take hold of ያዘ

holdings ንብረት

hole (v.) ቀደደ

hole, n. (of needle) ቀዳዳ ; (in a road) ቦርቦር ; (in an argument) ጉድለት

broke a hole በሳ

holiday በዓል፤ የዓመት፡ በዓል፡

holiness ቅድስና

His Holiness ብፁዕ

hollow out ቦረቦረ

hollow (n.) ጉድጓድ፡

hollow, adj. (wall) ክፍት ; (dish) ጎድጓዳ; (gourd) ባዶ ; (cheeks) የተጠበቀ (tree) የተቦረቦረ ; (promise) የማይጨበጥ

holocaust (destruction by fire)
የእሳት፡ መቃጠሉን
(wholesale destruction)
እልቂት

holy ቅዱስ

Holy Bible መጽሐፍ፡ ቅዱስ

Holy Communion ሥጋ፡ ወደሙ

Holy Ghost መንፈስ፡ ቅዱስ

holy orders ሥርዓተ፡ ቅስና፤ ተክህኖ

Holy Scripture መጽሐፍ፡ ቅዱስ

holy water ጠበል

homage አክብሮት
pay homage (formal acknowledgment) እጅ፡ ነሣ ; (pay respect) ምስጋና፡ አቀረበ

home (n.) መኖሪያ ; (country where one was born) ትውልድ አገር

home, adj. (town) የተወለደበት;
(products) ሀገር፡ ውስጥ፡ የተሠራ፡
home (adv.) እቤት፤ ወደ፡ ቤት
at home እቤት
feel at home እንደልቡ፡ ሊሆን፡ ቻለ

homeland ትውልድ፡ አገር

homeless ቤት፡ የሌለው

homemade ቤት፡ የተሠራ

home office ዋና፡ መሥሪያ፡ ቤት

homesick, be --- ናፈቀ(ው)፤ ዘመዶቹን፡ ናፈቀ

hometown የተወለደበት፡ ከተማ

homework የቤት፡ ሥራ፡

homily ድርሳን፡

homogenous አንድ፡ ዓይነት

homonym ተመሳሳይ

honest (person) ሐቀኛ ; (face) ታማኝ ; (opinion) እውነተኛ; (weights) ትክክለኛ

honestly በእውነት፡

honesty ታማኝነት፤ ሐቀኝነት

honey ማር

honeycomb የንብ፡ እንጀራ

honk (vt.) ነፋ
honk (vi.) ጮኸ

honor (v.) አከበረ ; (a check) ተቀበለ

honor (n.) ክብር ; (good name) ስም ; (act of respect) አክብሮት ; (case of esteem) ክብረት
guard of honor የክብር፡ ዘብ፡
His Honor ክቡር፤ የተከበረ
sense of honor ክብር

honorable (record) የሚያስከብር ; (intention) ቅን፡ የሆነ
(place) ወግ፡ ያለው

honorarium ገንዘብ

honorary የክብር

honored (adj.) የክብር

hood ቆብ ; (of car) ክዳን

hoodlum ዱርዬ

hoof ኮቴ

hook, vt. (a dress) ቈለፈ

(a fish) በመንጠቆ፡ ያዘ

hook, vi. (of dress) ተቈለፈ

(of road) ታጠፈ

hook (of lamp) መንጠቆ ; (for coat) ማንጠልጠያ ; (of telephone receiver) መስቀያ

by hook or by crook በዚህም፡ ሆነ፡ በዚያም

hookworm ወስፋት

hooligan ዱርዬ

hoot (v.) ጮኸ

hoot (n.) ጩኸት

not give a hoot ግድ፡ የለውም

hop ዘለለ

hop about (birds) ጡብ፡ ጡብ፡ አለ

(person) ዘለል፡ ዘለል፡ አለ

hope (v.) ተስፋ፡ አደረገ

hope (n.) ተስፋ

give up --- ተስፋ፡ ቈረጠ

hopeful (future) ተስፋ፡ የሚጣልበት

(words) ተስፋ፡ የተሞላበት

hopeless ተስፋ፡ የሚያስቈርጥ

hopscotch ሰኞ፡ ማክሰኞ ፤ እንክት፡ እንክቴ

horde መንጋ

horizon አድማስ ; (limit of one's knowledge) ዕውቀት

horizontal አግዳሚ

horn ቀንድ ; (wind instrument) መለከት ፤ ጥሩንባ

hornet ተርብ

horny የቀንድ ; (hands) ቆርፋዳ

horrible (sight) የሚያሰቀቅ

(weather, face) አስከፊ

horrid (behavior) በጣም፡ አስከፊ ፤

(climate) መጥፎ

horrify አሰቀቀ

horror (of war) ሠቆቃ ;

(strong dislike) ጥላቻ ;

(fright) ታላቅ፡ ድንጋጤ

horse ፈረስ

horseman ፈረሰኛ

horsepower የፈረስ፡ ጉልበት

horseriding ግልቢያ

horseshoe የፈረስ፡ የብረት፡ ኮቴ

horticulture የዕፀዋት፡ አበቃቀል

hose (tube) የውኃ፡ ቧምቧ

(stocking) የእግር፡ ሹራብ

hospice የእንግዳ፡ ማረፊያ

hospitable እንግዳ፡ ተቀባይ

hospital ሐኪም፡ ቤት ፤ ሆስፒታል

hospitality እንግዳ፡ ተቀባይነት

show hospitality አስተናገደ፡

hospitalized, be --- ሆስፒታል፡ ገባ

host (v.) ጋባዥ ፡ ነበረ

host (n.) እንግዳ፡ ተቀባይ ፤ ባለቤት

(heavenly) መላእክት

a host of ብዙ

hostage ጅሆ ፤ መያዣ፡

hostel ማረፊያ

hostess እንግዳ፡ ተቀባይ ፤ ባለቤት

hostile (territory) የጠላት

(attitude) የጥላቻ

hostility ጥላቻ

hostilities ጦርነት

hot (water) ሙቅ ; (weather) ሞቃት ; (pan) የጋለ

be hot (pepper) ተቃጨ

(with rage) ጦፈ

be red hot ጋመ

feel hot (air) ሞቀ

hothead ግልፍተኛ

hot-tempered ግልፍተኛ

hound (n.) አዳኝ፡ ውሻ

hotel ሆቴል

hour ሰዓት (any particular time) ጊዜ

all hours በማንኛውም፡ ሰዓት

for hours ለብዙ፡ ሰዓት

hour hand ሰዓት፡ ቈጣሪ

hourly, adj. (wage) በሰዓት፡ የሚያገኘው

hourly (adv.) በየሰዓቱ፡

house (v.) አኖረ

house (n.) ቤት ; (family) ቤተ፡ ሰብ

house of worship ቤተ፡ መቅደስ

around the house ቤት፡ ለቤት

keep house ቤት፡ አስተዳደረ

household ቤተ፡ ሰብ

housekeeper የቤት፡ ቀላቢት

housekeeping የቤት፡ አያያዝ

housemaid ገረድ

housewife የቤት፡ እመቤት

housework የቤት፡ ሥራ

housing መኖሪያ

hovel ደሳሳ፡ ጎጆ

hover አንዣበበ

how? እንዴት ፤ እንደምን

how እንዴት : እንደ + relative verb

how! እንዴት ፤ ምንኛ

how come? እንዴት

how far? እስከየት

how long? ምን፡ ያህል፡ ጊዜ

how many? ስንት

how much? ምን፡ ያህል

however ነገር፡ ግን

howl, v. (dog) አላዘነ; (wind) አፏጨ

howl (n.) ጩኸት

hub እምብርት

hubbub ግርግር

huddle (v.) አጐረ

huddle together እፍግፍግ፡ ብለው፡ ተቀመጡ፤ (in a corner) ተጠጋግተው፡ ቆሙ።

huddle (n.), go into a --- በቆየት፡ ተመካከሩ

hue ቀለም

hug, v. (hold fast) አቀፈ፡ አደረገ። አቅፎ፡ ያዘ

(keep close to) ተጠግቶ፡ ሄደ

huge (animal) ግዙፍ ; (box) ትልቅ፡

hull (v.) ፈልፈለ

hull, n. (of almond) ቅርፊት ; (of peanut) ገለባ ; (of ship) አካል

remove the hull ፈተገ

hum (of shepherd) አንጎራጎረ; (of bee) ጭዝ፡ አለ

human (n.) ሰው

human, adj. (body) የሰው፡ አካል; (liberty) የሰው፡ ልጅ

human being ሰው

humane ሰብአዊ

humanitarian (n.) በጎ አድራጊ

humanitarian (adj.) የበጎ፡ አድራጎት

humanity ሰው። የሰው፡ ልጅ

(kindness) ርኅራኄ

humanly እንደ ሰው

humble ትሑት ; (occupation) ዝቅተኛ ; (home) አልባሌ፡

humid እርጥበት፡ የበዛበት። እርጥበት፡ ያለው፡

be humid ረጠበ። ወበቀ

humidity ወበቅ፡

humiliate አዋረደ

~~humiliate ውርደት፤ እፍረት~~

humiliation ውርደት። እፍረት

~~humiliation~~

humility ትሕትና፡

humor (v.) አጫወተ

humor (n.) ቀልድ፡

be in bad humor ከፋ(ው)

be in a good humor ደስ፡ አለ(ው)

sense of humor ቀልደኛነት

hump ሻኛ፡

hump (v.), --- up (ground) አበጥ፡ አለ

hump one's back ጀርባን፡ ደፋ

hunch (hump) የጀርባ፡ መጕብጥ

(premonition) ግምት

have a hunch ተሰማ(ው)

hunchback ጉባጣ

hundred መቶ

hunger ረኀብ፣ ረሀብ

hungry የተራበ

be hungry ራበ(ው)

hunt አደነ ; (look for) ፈለገ

hunter አዳኝ

hunting ማደን፡

go --- አደን፡ ሄደ፡

hurdle (v.) ዘለለ

hurdle (n.) መሰናክል

hurl ወረወረ; (insults) አወረደ(በት)

hurricane ዐውሎ፡ ነፋስ

hurriedly ወዲያውኑ፣ በችኰላ

hurry (vt.) አጣደፈ ; (the work) በችኰላ፡ ሠራ፡

hurry (vi.) ተጣደፈ፣ ተፋጠነ፣ ችኰ፡ አለ፣ ቸኰለ፡

hurry (n.) ችኰላ፡

hurt (damage) ጐዳ፡ ; (cause pain) አሳመመ ; (one's feeling) አስቀየመ

husband ባል፣ ባለቤት

husbandry (farming) እርሻ; (of animals) እርባታ ; (careful management) አያያዝ

hush (vi.) ጭጭ፡ አለ፣ ዝም፡ አለ

hush! እሽ

hush (n.) ጸጥታ

husk (n.) ገንፋ

strip the --- ሸለቀቀ

husky (voice) ጎርናና ; (person) ጠብደል

hustle (vi.) ፈጠን፡ አለ፣ ተጣደፈ

hustle about ወዲያ፡ ወዲህ፡ ተሯሯጠ

hustle and bustle ግርግር

hut ጎጆ

hyena ጅብ

hygiene የጤና፡ ጥበቃ፡ ዘዴ፡

hymn መዝሙር

sing a hymn ዘመረ

hyphen ንኡስ፡ ጭረት

hypocrisy ግብዝነት

hypocrite ግብዝ

hypothesis ግምት፣ መላ፡ ምት

I

I እኔ

ice በረዶ

idea አስተያየት፣ አስተሳሰብ፣ ሐሳብ

← (purpose) ዓላማ

have an idea መሰለ(ው)

ideal (n.) ዓይነተኛ፡ አርአያ

(goal) ዓላማ

ideal (adj.) ተስማሚ (place) የሰላጠ

idealism የንልፎ፡ ኑሮ፡

identical ልክ፡ ያህን፡ የመሰለ

be identical ተመሳሰለ

identification መለያ፡ ነገር

identification card መታወቂያ፡ ወረቀት

identify ለየ ; (treat identical) አንድ፡ አድርጎ፡ አየ ;

(prove to be the same) አንድ፡ መሆኑን፡ አረጋገጠ

identity (sameness) ተመሳሳይነት; (who a person is) ማንነት

idiom ፈሊጥ፡ አነጋገር

idiot ደደብ፡

idle (vi.) ሥራ፡ ፈታ፡

idle away አባከነ፤ አጠፋ

idle, adj. (lazy) ሰነፍ

(not employed) ሥራ፡ ፈት

(useless) የማይረባ ፤ ከንቱ

be idle, lay idle ሥራ፡ ፈታ

idleness (laziness) ስንፍና

(not being employed) ሥራ፡ ፈትነት

idol ጣዖት

idolatrous ጣዖት፡ አምላኪ

idolatry የጣዖት፡ አምልኮ

practice idolatry ጣዖት፡ አመለከ

idolize አመለከ

if የ+ perfect እንደሆነ፤

ከ + perfect

ignite (vt.) አቀጣጠለ፤ አነደደ፡ አያያዘ

ignite (vi.) እሳት፡ ተያያዘ ፤ ነደደ ; (powder) ፈነዳ

ignoble (man) ወራዳ ; (defeat) የሚያሳፍር

ignominious አሳፋሪ

ignorance አለማወቅ ፤ አላዋቂነት

ignorant ደንቆሮ ; (answer) የሞኝን

ignore ቸል፡ አለ

ill (n.) በሽታ ; (evil) መቅሠፍት

ill (adj.), be --- አመመ (ው)

ill feeling ቅሬታ

ill luck መጥፎ፡ አጋጣሚ

ill manners ብልግና

ill will ክፉ፡ መንፈስ

fall ill ታመመ

speak ill of ክፉ፡ አነሣ

treat ill በደለ፡

illegal ሕገ፡ ወጥ

illegible የማይነበብ

illegitimate ሕገ፡ ወጥ

illegitimate child ዲቃላ

illicit የተከለከለ

illiteracy መሃይምነት

illiterate መሃይም

ill-mannered ባለጌ

illness ሕመም

illogical ከትክክለኛ፡ አስተሳሰብ፡ የወጣ

ill-tempered ቁጡ

ill-treat (a horse) አንገላታ፤ አንገላቀለ; (a child) በደለ

ill-treatment በደል

illuminate ብርሃን፡ ሰጠ

(a passage) አብራራ ; (with paintings) በሥዕል አስጌጠ

illumination (of a theory) ማብራሪያ

illusion የተሳሳተ፡ እምነት

illustrate (with drawings) ለመግለጫ፡ ፈሆን፡ ዘንጭ፡ ሣለ;

(with an example) አብራራ

illustration ሥዕል ; (with example) ማብራሪያ

illustrator ሠዓሊ

illustrious ገናና፤ ስመ፡ ጥሩ

image አምሳል ; (thing seen in a mirror) መልክ ; (idea) ሐሳብ

imaginary ሐሳብ፡ የወለደው፤ በሐሳብ፡ የወጣ

imagination ቅዶና፡ ኅሊና

imagine በሐሳብ፡ ፈጠረ

(think) መሰለ(ው)

imbecile ጅል

imbibe መጠጠ

imitate ቀዳ ; (mimic) እያስመሰለ፡ ቀለደ፡

imitation ቅጅ ; (something not real) ሰው፡ ሠራሽ

immaculate (clothes) ፍጹም፡ ንጹሕ;

(conduct) እንከን፡ የሌለው

immaculate life ብቃት

immaterial, be --- (not consisting of matter) ግዙፍ፡ አይደለም

(be unimportant) ግድ፡ የለውም

immature ያልበሰለ

immeasurable ወሰን፡ የሌለው

immediate የተፋጠነ፤ ፈጣን፡ ድክ

(family, neighbor) የቅርብ

immediately አሁኑኑ፤ ወዲያውኑ

immense (room) በጣም፡ ሰፊ

(building) ግዙፍ

immensely እጅግ፡ በጣም

immerse ነከረ

immigrant ስደተኛ

immigration ስደት

imminent, be --- የማይቀር፡ ነው

immobile, remain --- ቀጥ፡ ብሎ፡ ቆመ

immodest ትሕትና፡ የጐደለው ; (dress) አስነዋሪ

immoral ከግብረ፡ ገብነት፡ ውጪ፡ የሆነ፡

immortal ሕያው; (reputation) ሕያው፡ ስም፡ ያለው

immortality ሕያውነት

immovable (stubborness) የማይበገር

be immovable (earth) አልተንቀሳቀሰም

immovables የማይንቀሳቀስ፡ንብረት

immune, be --- to (a disease)
ከ ... መዳን፡ነው

impact ኃይል ; (collision) ግጭት ;
(influence) ተጽዕኖ

impair ጎዳ

impartial አድሎ፡የሌለበት

impassable, be --- (ford)
አያሻግርም ; (road)
አያስኬድም

impatience ትዕግሥት፡ማጣት

impatient, be --- ትዕግሥት፡
አጣ ; (eager) ጓጓ

impatiently (eagerly) በጉጉት ;
(not patiently) ትዕግሥት፡
በማጣት

impeccable እንከን፡የሌለው

impede አገደ

impediment መሰናክል ፤ ዕንቅፋት

impel (drive forward) ገፋ ;
(force) አስገደደ

impend (of war) ሊነሣ፡ሊል ;
(of death) አይቀርም

impenetrable የማይደረስበት

imperative (n.) ትእዛዝ፡አንቀጽ

imperative (adj.) የትእዛዝ

imperfect የተበላሸ ;
(knowledge) ያልተሟላ

imperial የንጉሠ፡ነገሥት
His Imperial Majesty
ግርማዊ፡ንጉሠ፡ነገሥት

imperialism ኢምፔሪያሊዝም

imperil አደጋ፡ላይ፡ጣለ ፤ አደጋ፡
አደረሰ

imperious እብሪት፡የተሞላበት

imperishable የማይበላሽ

impersonate (act the character
of) እንደ ... ሆኖ፡ሠራ ; (pretend
to be) መስሎ፡ታየ

impertinence ብልግና

impertinent (child) ስድ፡አደግ ;
(remark) የማይገባ

impetuous (child) ቸኩል ;
(wind) ኃይለኛ

impetus ኃይል

implacable (enemies) የምር ;
(anger) የማይበርድ

implement (v.) ሠራ ፤ ፈጸመ

implement (n.) መሣሪያ

implicit (threat) ውስጣዊ
(consent) ያልተገለጸ

implore ለመነ

imply በተዘዋዋሪ፡መንገድ፡ጠቀሰ

impolite ባለጌ

import (v.) አስመጣ ፤ ከውጭ
አገር፡አስመጣ

import, v. (merchandise) ወደ፡
አገር፡ውስጥ፡የገባ፡እቃ

(meaning) ፍሬ፡ ነገር

importance ጥቅም፤ ጠቃሚነት፤ ዋጋ

important (matter) ከፍተኛ፤ ብርቱን

(person) ታላቅ ; (speech) ጠቃሚ

be important ተፈላጊነት፡ አለው፤ ዋጋ፡ አለው፡

importune ወተወተ

impose ጣለ

be imposed (duties) ተጨመረ

impose on (bother) አስቸገረ ; (force) አስገደደ

imposing ግርማ፡ ያለው

imposition (of a tax) መጣል ; (imposing on someone by taking advantage of his nature) ማስቸገር፡

impossible የማይሆን

be impossible አይቻልም

imposter አጭበርባሪ

impotent, be --- ጉልበት፡ አልነበረውም፤ ችሎታ፡ አልነበረውም

impound በሕግ፡ ያዘ

impoverish አደኸየ

impractical ሊሠራ፡ አይቻልም

imprecation እርግማን

impregnable የማይበገር

impregnate ጨመረ(በት)

impress (v.) አስደነቀ፤ አስገረመ

(stamp) ቀረጸ

impression (of heel) ዱካ ; (of fingerprint) አሻራ ; (of seal) መቅረጽ

be under the impression መሰለ(ው)

leave an impression ስሜት፡ አሳደረበት፡

impressive አስደናቂ

imprint (of foot) ዱካ

(mark) ምልክት

imprinted, be --- (with a seal) ታተመ ; (in one's memory) ተቀረጸ

imprison አሰረ

imprisonment እስራት

improbable የማይመስል

improper ትክክለኛ፡ ያልሆነ፤ የማይገባ

improve(vt.) አሻሻለ

improve(vi.) ተሻሻለ

improvement መሻሻል

improvise (words) ፈጠረ

imprudent አስተዋይነት፡ የጎደለው

impudence ብልግና

impudent ባለጌ፤ ዓይን፡ አውጣ

impulse (feeling) ስሜት

(of wind) ግፊት

impulsion	ግፊት
impulsive	በስሜት፡ የሚገፋፋ
impure	ቆሻሻ ፤ ያልተጣራ;
(air)	የተበላሸ
in	በ ፤ በ... ውስጥ ፤ እ... ውስጥ
inability	ያለመቻል
inaccuracy (error)	ጉድለት ;
(lack of accuracy)	አለመስተካከል
innacurate, be ---	ትክክለኛ፡ አይደለም
inaction	ስንፍና
inactive (volcano)	ሙት
be inactive	አልሠራም
inadequate, be ---	አይበቃም፡
inadvertent	ባለማወቅ፡ የተደረገ
inane	ጅላጅል
inanimate	ግዑዝ
inapplicable, be ---	አግባብነት፡ የለውም
inappropriate	የማይገባ
inapt	ተገቢ፡ ያልሆነ
inarticulate (groan)	የማይለይ;
(speaker)	የማይወጣለት
be inarticulate	አይናገርም
inattentive	የማይከታተል
inaugural	የምረቃ
inaugurate	መረቀ
inauguration	የምረቃ፡ ሥነ፡ ሥርዓት

inauspicious	ገደ፡ ቢስ
inborn	የተፈጥሮ
inbred, be ---	እርስ፡ በርሳቸው፡ ተጋቡ
incantation	ድግምት
incapable	የሥራ፡ ችሎታ፡ የሌለው
incapacitate	ከለከለ
be incapacitated	ስንኩል፡ ሆኖ፡ ቀረ
incarcerate	አሰረ
incarnation	ሥጋ፡ መልበስ
be the incarnation of	ተመሰለ
incendiary (bomb)	የእሳት ;
(article)	ሕዝብ፡ የሚያነሣሣ
incense (v.)	አበሳጨ
be incensed	ጠላ
incense	ዕጣን
incentive	የሚገፋፋ
inception	መጀመሪያ
incertitude	እርግጠኛ፡ አለመሆን፡
incessantly	ያለማቋረጥ
inch	ኢንች
incident	ድርጊት ፤ አጋጣሚ
(conflict)	ግጭት
incidental (expenses)	ልዩ ;
(remark)	ቀለል፡ ያለ
incidentally	እንደአጋጣሚ
incinerate	አቃጠለ
incise	ቀረጸ

incision ቀዶ፡ ጥገና

incisive ጥልቅ

incisor የፊት፡ ጥርስ

incite አነሣሣ

inclemency (of weather)
መጥፎነት

inclement (ruler) ጨካኝ

(weather) መጥፎ፡

inclination (bending) ደፋ፡ ቀና፡
ማድረግ፡ ; (preference)
ዝንባሌ

incline (vt. አዘነበለ

incline (vi.) አጋደለ

be inclined ዝንባሌ፡ አለው

include ጨመረ፤ አጠቃለለ

included (adj.) አብሮ የተያያዘ

including ከነ ... ጋር

incognito ማንነቱን፡ ሳያሳውቅ

incoherent ተከታታይነት፡ የሌለው

incombustible የማይቃጠል

income ገቢ

incoming አዲስ

incomparable ወደር፡ የሌለው

incompatible, be --- ተስማሚ፡
አይደለም፡

incompetent ችሎታ፡ የሌለው

incomplete, be --- የተሟላ፡ አይደለም

incomprehensible, be ---
አይገባም

inconceivable የማይታመን

incongruous, be --- አይስማማም

inconsistent ተለዋዋጭ

inconspicuous (hat) ዓይን፡
የማይማርክ፤(part in a play)
አጉሌ፡ የማያስኝ

inconvenience (v.) አስቸገረ

inconvenience (n.) ችግር

inconvenient የማይመች

incorrect ትክክል፡ ያልሆነ

incorrigible የማይታረም

incorruptible የማይታለል

increase (vt.) ጨመረ ;
(productivity) ከፍ፡ አደረገ

incredible የማይመስል

increment ጭማሪ

incriminate ጥፋተኝነትን፡ አመለከተ

incubate ተፈለፈለ

incumbent, be --- on (upon) ግዴታው፡
ነው፤ ተገቢ፡ ነው፡

incurable የማይፈወስ፤ የማይድን፡

incursion ወረራ

make an incursion በዘበዘ

indebted, be --- to (for help)
ባለውለታው፡ ነው፡
(for money) የ ... ገንዘብ፡ ባለዕዳ

indecent የብልግና

indecisive, be --- ውሳኔ፡ አልሰጠም

indeed በእውነቱ፤ በእርግጥ

indefinite ያልተወሰነ

indefinite article ያልተወሰነ፡
መስተ ኣምር፡

indelible (ink) የማይለቅ

indemnify ገንዘብ፡ ሰጠ

indemnity ካሳ

independence ነጻነት

independent ነጻ ; (mind)
በራሱ፡ አሳብ፡ የሚመራ

be independent (on one's own)
ራሱን፡ ቻለ

indestructible የማይበላሽ

indeterminate ለግንግል፡ ያልታወቀ

index finger ሌባ፡ ጣት

India ህንድ

indicate አመለከተ፤ አሳየ

indication ምልክት ; (hint) ፍንጭ

indict ከሰሰ

indifference ግዴለሽነት፤ ቸል፡ ማለት

indifferent የግዴለሽነት

be (remain) indifferent
ግድ፡ የለሽ፡ ሆነ፡

indigence ድኽነት

indigent ምስኪን

indigestible, be --- አይዋሐድም

indigestion, give --- ሆድን፡
ጎረበጠው.

indignant, be --- ተናደደ

indirect ቀጥተኛ፡ ያልሆነ፡

indiscriminate (bombing) እሹ፡
እንደመጣ

indispensable አስፈላጊ

indisposed, be --- ጤና፡ አይሰማም

be indisposed to ዝንባሌ፡
የለውም

indistinct (noise) የማይለይ

(signature) የማይነበብ፡

individual (adj.) የግል፤ የራስ

individually በየግል፤ አንድ፡ ባንድ፡

indivisible ሊከፋፈል፡ የማይቻል

indoctrinate አሳመነ

indolence ስንፍና

indolent ሰነፍ፡

indoors እቤት፤ እቤት፡ ውስጥ

induce አግባባ

inducted, be --- (into the army)
ተከተበ

indulge አንከባከበ

indulgent ልል

industrious (worker) ታታሪ

industry ኢንዱስትሪ

inebriate አሰከረ

inedible, be --- አይበላም

ineffective, be --- አጥጋቢ፡ ያልሆነ

inefficient አጥጋቢ፡ ውጤት፡ የማይሰጥ

ineligible, be --- (unqualified)
~~ተገባ~~ አይደለም፡

ተገቢ፡ አይደለም ; (not eligible) መብት፡ የለውም

inept (person) ሙያ፡ የሌለው

(remark) ተገቢ፡ ያልሆነ

inequality መበላለጥ ፤ አለመስተካከል

inert ግዑዝ

inevitable የማይጠረጠር፤ የማይቀር

inexact ትክክል፡ ያልሆነ

inexcusable የማይታለፍ

inexhaustible የማያልቅ፡

inexistent, be --- የለም

inexpensive ርካሽ

inexperienced የሥራ፡ ልምድ፡ የሌለው

inextricable መውጫ፡ የሌለው

infallible የማይሳሳት

infamous አስነዉ፡

infamy መጥፎ ስም፡

infancy የሕፃንነት፡ ጊዜ

infant ሕፃን

infantile (disease) የልጆች

(behavior) የሕፃንነት

infantry የእግረኛ፡ ጦር፡

infect መረዘ ; (spoil) አበላሸ

infection የቁስል፡ መመርቀዝ

infectious በሽርም፡ የሚይዝ

infer አመሳከተ፡

inferior (position) ዝቅተኛ ; (quality) ሀገኛ

infest ወረረ

infidel አረመኔ

infidelity ቃል፡ ኪዳን፡ ማፍረስ

infiltrate ሰርጎ፡ ገባ ፤ ሾልኮ፡ ገባ፡

infiltrator ሰርጎ፡ ገብ፡

infinite የማይወሰን፤ መጠን፡ የሌለው፡

infinitely አለቅጥ

infirm ደካማ

infirmary ክሊኒክ

infirmity ድካም፡ ምስኪንነት

inflame (make red) አቀላ ;

(make the sky red) ደም፡ አስመሰለ; (arouse) አስቆጣ

inflammable ነዳጅ

inflammatory የሚያስቆጣ

inflate ነፋ፡

inflation የገንዘብ፡ ዋጋ፡ መውረድ

inflect አረባ

inflection (rise and fall in the voice) የድምፅ፡ አነባበር ;

(of verb) አረባብ

inflexible (law) ጥብቅ፡ የማይለ ;

(determination) የማይናወጥ

influence (v.) አግባባ ፤ ተጽዕኖ፡ አሳደረ፡

influence (n.) ተጽዕኖ ፤ ተሰሚነት

influential ተደማጭነት፡ ያለው፡

influx በብዛት፡ መግባት

inform አስታወቀ ፤ ነገረ

informal (discussion) አፊሲቆል፡

~~ያልሆነ~~

ያሰሠኘ ; (party) ~~[illegible]~~
መግቢ:

information መረጃ ፤ መግለጫ;
(Knowledge) ዕውቀት
Ministry of Information
የማስታወቂያ: ሚኒስቴር

information desk መረጃ: ክፍል

informer ጆሮ: ጠቢ ፤ ወሬ: አቀባይ

infraction መጣስ

infrequently አልፎ: አልፎ:

infringe ጣሰ

infuriate አናደደ

infuse (steep in a liquid)
ዘፈዘፈ ; (inspire) አነቃቃ

ingenious (person) ብልህ;
(device) በጣም: የረቀቀ

ingenuity ብልህነት

ingenuous የዋህ

ingrained ሥር: የሰደደ

ingratitude ውለታ: ቢስነት

ingredient ቅመማ : ቅመም:

inhabit ኖረ

inhabitant ነዋሪ

inchale አየር: ወደ: ውስጥ: ሳበ

inherent የተፈጥሮ:

inherit ወረሰ

inheritance ውርስ

inhospitable አስተናጋጅነት:
የጎደለው:

inhuman ሰብአዊ: ያልሆነ

inimical (showing hostility)
የጥላቻ ; (harmful) ጎጂ

iniquitous የግፍ

initial (n.) የስም: መጀመሪያ: ፊደላት

initial (adj.) የመጀመሪያ

initiate (a plan) ጀመረ ; (help
a person in something new)
አስለመጠ

initiative ሐሳብ: የማመንጨት: ችሎታ

inject (give an injection)
መርፌ: ወጋ;
(introduce) ጣልቃ: አስገባ

injection መርፌ:

injunction (of father) ትእዛዝ;
(of court) የፍርድ: ቤት: ማገጃ

injure ጎዳ ; (spoil) አበላሸ ;
(reputation) አጎደፈ
be injured ቆሰለ

injury ጉዳት ፤ ቁስል

injustice በደል ፤ የግፍ: ሥራ
do injustice በደለ

ink ቀለም

inkling ፍንጭ

inkpad የቀለም: ማኅተም ጠጫ:

inland (adj.) ገባ: ያለ:
inland (adv.) ወደ: መሃል: አገር

in-laws አማቶች:

inlet ትንሽ: ሰላጤ

inmate (of prison) እስረኛ;
(of hospital) ሃቆሬ: በሽተኛ:

innost (desire) የልብ: ;
(depth) የመጨረሻ:

inn ፓንሽ: ሆቴል

innate የተፈጥሮ:

inner (door) የውስጠኛ;
(thought) የልብ

innermost የመሃከለኛ:

innocence ንጹሕ: መሆን ፤ ጥፋተኛ:
አለመሆን: ; (ignorance)
አለማወቅ

innocent ንጹሕ ; (without
knowledge of evil) የዋሀ

innocuous (remark) የማያስከፋ
be innocuous (snake)
መርዘኛ : አይደለም

innovate (vt.) አሁን: አመጣ
innovate (vi.) አዲስ. ዘዴ: ፈጠረ

innovation አዲስ: ነገር

innumerable ቁጥር: ስፍር: የሌለው:

inoculate ክትባት: አደረገለት

inoculation ክትባት

inoffensive (manner)
የማያስቀይም

inoperative, be --- ከአገልግሎት.
ውጪ. ሆነ:

inopportune የማይመች

inquest ምርመራ

inquire ጠየቀ
inquiry ምርመራ

inquisition ምርመራ.

inquisitive ተመራማሪ:

insane እብድ ፤ የአእምሮ: ሕመምተኛ:
be insane አበደ

insanitary ለጤና: ጠንቅ

insanity እብደት ፤ አንጎል: መታወክ:

insatiable (curiosity) የማይረካ
be insatiable (appetite)
አልጠግብም

inscribe ቀረጸ

inscription ጽሑፍ

insect ነፍሳት

insecure የማያስተማምን:
feel insecure ፍራቻ: አደረ(በት)

insensible, be --- of አላወቅም:
be insensible to አልተሰማውም

inseparable የማይለያይ

insert አስገባ ; (into
the pocket) ከተተ

inside (n.) ውስጥ

inside (adj.) የውስጥ

inside (prep.) ከ ··· ውስጥ
inside (adv.) ·· እ ውስጥ

insidious (plan) የተንኮል ;
(remark) ተንኮልን: ያዘለ

insight, get an --- ጠልቆ፡ ዐወቀ

insignia አርማ

insignificant (role) አነስተኛ;

(details) የማይረባ

insincere ከንፈር፡ በስቶ

insinuate በእግባ፡ ተናገረ፡

insinuate oneself into

ተሸሞጥሙጦ፡ አገኘ፡

insipid, be --- ጠዐም፡ የለውም

insist ድርቅ፡ አለ

insistence ችክ፡ ማለት

insistent, be --- ድርቅ፡ አለ

insolence ብልግና

insolent ባለጌ፡

insoluble, be --- (of grease)

አይቀልጥም;

(of a mystery) ማወቅ፡ አልተቻለም፡

insomnia የእንቅልፍ፡ እጦት፡

inspect (troops) ጎበኘ ;

(baggage) ፈተሸ

inspection ፍተሻ

inspector ተቆጣጣሪ

inspiration (stirring of feelings)

የሚያነሣሣው፡ መንፈስ

(bright idea) ድንቅ፡ ሐሳብ ;

(drawing of air into the lungs)

መተንፈስ

be an inspiration አነቃቃ

give inspiration አነሣሣ

inspire (arouse to action)

ቀሰቀሰ ; (stir deeply)

መንፈሱን፡ አነሣሣ

install አቋመ ; (telephone) ቀጠለ

installation ድርጅት

installment (of a story) ተከታታይ፡

እትም; (partial payment)

የጊዜ፡ ክፍያ፡

instance (case) ማስረጃ፡

(example) ምሳሌ

for instance ለምሳሌ

instant, at that --- በዚያን፡ ጊዜ

this instant አሁኑኑ፡

instantly ባንድ፡ አፍታ፡

instead በሱ፡ ፈንታ፡

instead of በ ... ምትክ፤

በ ... ፈንታ፡

instigate አነሣሣ

instill አሳደረ

instinct የተፈጥሮ፡ ስሜት፤ ተፈጥሮ

institute, v. (laws) ደነገገ ;

(a course) ጀመረ

institute ኢንስቲቱት

institution ድርጅት ; (custom)

ልማድ ; (establishing)

መቋቋም

instruct (inform) አስታወቀ ;

(teach) አስተማረ; (order) አዘዘ

instruction ትምህርት

instructions (direction) መምሪያ ; (order) ትእዛዝ

instructive, be --- ትምህርት: ሰጠ ፤ ትምህርት: ተገኘበት

instructor አስተማሪ

instrument መሣሪያ

insubordinate የማይታዘዝ

insubordination አለመታዘዝ

insufficient, be --- በቂ: አይሆንም

insular (related to an island) የደሴት ; (narrow-minded) ጠባብ

insult (v.) ሰደበ

insult (n.) ስድብ ፤ ዘለፋ፡

insurance የሕይወት: ዋስትና፡

insure ዋስትና: አስገባ

(make sure) አረጋገጠ

insurgency ዐመፅ

insurgent ዐመፀኛ

insurrection ሁከት

intact ሳይሰበር

intangible የማይዳሰስ

integral (essential) ዋይነተኛ

(entire) ጠቅላላ

integrate አዋሐደ

integrity (honesty) ሐቀኝነት; (wholeness) አንድነት

intellect የማሰብ· ችሎታ

intellectual (n.) ምሁር

intelligence አእምሮ ፤ የማሰብ: ችሎ

intelligent ብልህ

intelligible, be --- (noise) ጎልቶ: ተሰማ ; (response) መረዳት: አላስቸገረም:

intemperate (winter) ኃይለኛ ; (language) ያልተገታ ; (given to excessive drinking) ከመጠን: በላይ: የሚጠጣ:

intend አሰበ፡

intended (adj.) የታቀደ

be intended (of a remark) ተሰነዘረ ; (of money) ተመደበ

intense (heat) ኃይለኛ ; (strong in feeling) የጋለ: ስሜት· ያለው፡

intensify (effort) አጠናከረ ; (studies) ጠበቅ: አደረገ

intensity (of heat) ኃይል; (of anger) ግለት

intensive በጥንቃቄ፡ የተደረገ

intent (n.) ዓላማ፡

intention አሳቢያት ፤ ዓላማ

intentionally ሆን፡ ብሎ

intently በጥንቃቄ፡

intercalate አስገባ፡

intercede አማለደ

intercession አማላጅነት

interchange (v.) አቀያየረ፤ አለዋወጠ

interconnect ተገናኘ

intercourse ግንኙነት

interdict ከለከለ

interdiction ማገድ፡

interest (v.) ፍላጎት፡ አነሣሣ;

(attract) ሳበ

be interested in ወደደ፤ ፈለገ፤ ፍላጎት፡ ነበረው፡

interest (n.) ፍላጎት ; (hobby) የሚወደው፡ ነገር ;

(share) ጥቅም ; (money paid on a loan) ወለድ

take an interest in በሙሉ፡ ልብ፡ ተቆጣጠረ፡

interesting የሚያስደስት

interfere (meddle) ጣልቃ፡ ገባ ;

(come into opposition) አጋጠመ(ው)

interim ጊዜያዊ

interior (n.) ውስጥ

Ministry of Interior የአገር፡ ግዛት፡ ሚኒስቴር፡

interior (adj.) የመኻል

(domestic) ያገር፡ ውስጥ

interject ወረወረ፡ አደረገ

interjection ቃለ፡ አጋኖ፡

interlace አቈላለፈ

interline በመሥመሩ፡ መኻከል፡ ጻፈ

interlocutor በውይይት፡ አብረውት፡ ተካፋይ፡

interlude የዕረፍት፡ ጊዜ፡

intermarry ተጋባ፡

intermediary (n.) አስታራቂ

intermediary (adj.) መኻከለኛ

(serving to mediate) አስታራቂ

intermediate መኻከል፡ ያለ

interminable ማለቂያ፡ የሌለው

intermingle (vt.) አደባለቀ፤ ቀላቀለ

intermission የዕረፍት፡ ጊዜ

without intermission ያለ፡ ፋታ

intermittently አልፎ፡ አልፎ

intern (v.) አስጠበቀ

internal የውስጥ፤ ውስጣዊ

international ዓለም፡ አቀፍ

internist የውስጥ፡ አካል፡ ሐኪም፡

interpose, vt. (an objection) በመኻከል፡ አቀረበ፡

(one's body) በ··· መሀከል፡ አደረገ

interpose~~d~~ (vi.) ጣልቃ፡ ገባ፡

interpret አስተረጐመ ; (a dream) ፈታ; (read a meaning into) ቈጠረ

interpretation (of behavior) ፍች ;

(of a poem) ማብራሪያ; (by an actor) አቀራረብ፡

interpreter አስተርጓሚ

interrelate አቀናበረ

interrogate መረመረ

interrogation ምርመራ

interrogative pronoun መጠይቅ ተውላጠ፡ ስም

interrupt አቋረጠ

interruption መቋረጥ

without interruption ሳያቋርጥ

intersect ተላለፈ

intersection መገናኛ ፤ የመንገዶች : መገናኛ

intertwine ተጠላለፈ

interval ዕረፍት ; (space between objects) ክፍት፡ ቦታ

at intervals አልፎ፡ አልፎ

intervene አማለደ

intervention ገላጋይነት ፤ አማላጅነት

interview (v.) የቃል፡ ጥያቄ፡ አቀረበ

interview (n.) የቃል፡ ጥያቄ

intestinal የአንጀት

intestine አንጀት

intimacy የቅርብ፡ ግንኙነት

intimate (v.) ጠቆመ

intimate (n.) የቅርብ፡ ወዳጅ

intimate, adj. (friend) የቅርብ; (knowledge) የጠለቀ; (gathering) የወዳጆች

intimately, be --- acquainted with (a person) በቅርብ፡ ተዋወቀ (a subject) የጠለቀ፡ ዕውቀት አለው

intimidate አስፈራራ

into ወደ ፤ ውስጥ

intolerable የማይቻል

intolerance አለመቻቻል

intolerant የማይቋቋም ፤ የማይቀበል ፤ የማይደግፍ

intonation (of prayer) ዝማሬ ; (of a question) የቃል፡ አነባበር

intone አዜመ

intoxicate አሰከረ

intransigent ሐሳበ፡ ግትር

intransitive የማይሻገር

intrepid ደፋር

intricate (ideas) የተወሳሰበ ; (design) የረቀቀ

intrigue, v. (plot) አሴረ ፤ አደመ (fascinate) ሳበ ፤ ማረከ

intrigue (n.) ሴራ ፤ ተንኰል

introduce ለመጀመሪያ፡ ጊዜ፡ አስመጣ; (a bill) አቀረበ ; (make know) አስተዋወቀ ; (insert) ከተተ ፤ አስገባ

introduction መግቢያ

introductory የመግቢያ

intrude ጣልቃ፡ ገባ፡

intrusion (into a residence) መግባት ; (into a conversation) ጣልቃ፡ ገብነት

intrusive ጣልቃ፡ ገብ፡

intuition ስሜት

inundate አጥለቀለቀ

invade (attack) ወረረ; (encroach on) ጣልቃ፡ ገባ

invader ወራሪ

invalid (n.) አካለ፡ ስንኩል፡ ሰው

invalid (adj.), be --- አልጸናም

invalidate ሻረ

invaluable በገንዘብ፡ የማይገኝ

invariable የማይለዋወጥ

invasion ወረራ

invent (devise something new) ፈለሰፈ ; (fabricate, devise) ፈጠረ

invention (creation) ፍልሰፋ; (something made up) ፈጠራ

inventor ፈልሳፊ

inventory ዝርዝር

inverse ተቃራኒ

inversion ግልብጥ

invert ገለበጠ ; (a glass) ደፋ

invest (money, time) አወጣ፡ አዋለ; (give) ሰጠ; (install in office) ሹመት፡ ሰጠ

investigate መረመረ

investigation ምርመራ

investment ገንዘብ፡ ማዋል

inveterate (liar) የተፈጥሮ; (smoker) የጸና፡ ሱስ፡ ያለበት፡ ሰው፡

invidious አስከፊ፡

invigorate አበረታ

invincible የማይበገር

inviolable የማይጣስ

inviolate የማይነካ

invisible, be --- አይታይም

invitation ግብዣ ; (written permission) የጉዞ፡ ወረቀት

invite ጠራ ; (attract) አጓጓ

invite in ግባ፡ አለ

invite to dinner ጋበዘ

invocation ልመና፡ ማቅረብ

invoice ፋክቱር

invoke ለመነ

involuntary ያለውዴታው፡ የተደረገ

involve (result in) አስከተለ; (require) ጠየቀ ; (mix up) ጣለ ; (include) አጠቃለለ (touch) ነካ

involved (adj.) የተወሳሰበ

be involved in ተካፋይ፡ ሆነ

inward (adj.) ውስጣዊ

inward (adv.) ወደ፡ ውስጥ

inwardly ውስኝ፡ ውስጠኝ፡

irascible ግልፍተኛ

irate የተናደደ

ire ቁጣ

arouse ire አስቆጣ

irk ቅር፡ አሰኘ

irksome የሚያስከፋ

iron (v.) ተኮሰ

iron, n. (metal) ብረት ; (ironing press) ካውያ

ironical የምፀት፤ የዘበት

ironing press ካውያ

irony ምፀት

irrational (fear) መሠረት፡ ቢስ

irreconcilable ዕርቅ፡ የማይገባው

irrefutable የማይካድ

irregular (not according to rules) ሥርዓቱን፡ ያልተከተለ፤ ከተለመደው፡ የወጣ; (not even) ወጣ፡ ገባ

irrelevant, be --- ግንኙነት፡ የለውም፤ አግባብ፡ የለውም

irreligious ሃይማኖት፡ ቢስ

irreplaceable ምትክ፡ የማይገኝለት

irreproachable እንከን፡ የሌለው

irresistible (an attack) ለመቋቋም፡ የማይቻል

irresolute ወላዋይ

irresponsible (not responsible) ግዴ፡ የለሽ ; (not to be depended upon) እምነቱን፡ የማይጠብቅ፡

irreverent አክብሮት፡ የጐደለው

irrevocable የማይሻር

irrigate በመስኖ፡ አጠጣ

irrigation መስኖ

irritable ግልፍተኛ

be irritable ቁጣ፡ ቁጣ፡ አለ; (skin) ተቆጣ

irritate አበሳጨ፤ አናደደ፤ አስቆጣ ; (the skin) አስቆጣ

is, he --- (quality) ነው ; (presence) አለ

Islam እስልምና፤ እስላም

island ደሴት

isolate ከሌሎች፡ ለየ; (a sick person) ለይቶ፡ አስተኛ

isolated (adj.) ገለልተኛ

be isolated (sick children) ከሌሎች፡ ተገለለ

(a military unit) ተነጠለ

isolation ለብቻ፡ መሆን

issue, v. (distribute) ዐደለ ; (publish) አወጣ

issue, n. (matter) ጉዳይ ; (result) ውጤት ; (publication) እትም ; (descendence) ዘር

Italian ኢጣሊያን ; (language) ኢጣሊያንኛ

Italy ኢጣልያ

itch, v. (wound) እከከ: (shirt) ኰሰኰሰ

itch (n.) እከክ

item እቃ ; (piece of news) ወሬ

itemize ~~[illegible]~~ ዘረዘረ

iterate ~~[illegible]~~ ደጋገመ

itinerant ተዘዋዋሪ

itinerary ጉዞ

itself ብቻውን

by itself (alone) [illegible]

ivory የዝሆን፡ ጥርስ

ivy ሐረግ

J

jab ወጋ

jack ክሪክ

jackal ቀበሮ

jackass ወንድ፡ አህያ

jacket ጃኬት

jail (v.) አሰረ

jail (n.) እስር፡ ቤት፤ ወህኒ፡ ቤት

jam, v. (place forcibly) ሰነቀ; (pack tightly) አጨቀ ; (of cars) አጨናነቀ

jam, n. (preserve) ማርማላታ; (traffic) መተፋፈግ

janitor ጠባቂ

January ጥር

Japan ጃፓን

jar, vt. (cause to shake) አነቃነቀ; (cause a shock to) ክው፡ አደረገ

jar, vi. (produce a harsh sound) ሲጢጥ፡ አለ; (come into conflict) ተጋጨ

jar (n.) ማሰሮ፤ ገንቦ

jargon ልዩ፡ ቋንቋ

jaundice የወፍ፡ በሽታ

javeline ጦር

jaw አገጭ

jawbone መንጋጋ

jealous ቀናተኛ

be --- ቀና

jealousy ቅናት

jeer (v.) ሣቀ(በት) ; (shout mockingly at) ጮኸ(በት)

jeer (n.) የፌዝ፡ ሣቅ

jeopardize (a chance) አጨናገፈ; (one's life) ገደል፡ ላይ፡ ጣለ

jerk አንጠዘ በድንገት፡ ጎተ

jest (v.) አፌዘ

jest (n.) ቀልድ

jester አፌዘኛ

jet ጀት፡ አውሮፕላን

Jew አይሁዳዊ

jewel የከበረ፡ ድንጋይ፤ ፈርጥ

jeweler አንጥረኛ

jewelry ጌጣጌጥ

jilt ከዳ

jingle (vt.) አንቃጨለ

jingle (n.) መቃጨል

job ሥራ

jobless ሥራ፡ ፈት

jocose የቀልድ

jocular (person) ቀልደኛ

(reply) የፌዝ

jocund ሣቂታ

jog ነካ፡ አደረገ

join (vt.) አገጣጠመ ; (unite with) ከ... ጋር፡ ተቀላቀለ

(a couple in marriage) አስተሳሰረ ; (come into the company) አብሮት፡ ሄደ

join, vi. (become united) ተገናኘ ; (participate) ተካፋይ፡ ሆነ

joint, n. (of finger, bamboo)

~~አንጓ~~

አንጓ ; (part where two bones join) መገጣጠሚያ

joint (adj.) የጋራ

jointly የጋራቸው

joke (v.) አፌዘ፤ ቀለደ

joke (n.) ቀልድ

joker ቀልደኛ

jolly (person) ደስተኛ; (time) የደስታ

jolt አንገጫገጨ

jot, --- down ጻፈ

journal መጽሔት ; (diary) ማስታወሻ

journalist ጋዜጠኛ

journey (v.) ተጓዘ

journey (n.) መንገድ፤ ጉዞ

go on a --- ተጓዘ

jovial ደስተኛ

joy ደስታ

joyful አስደሳች

joyous የሚያስደስት

jubilance ፈንጠዝያ

jubilant በደስታ፡ የተሞላ

jubilee ኢዮቤልዩ

Jubilee Palace የኢዮቤልዩ፡ ቤተ፡ መንግሥት

judge (v.) ፍርድ፡ ሰጠ፤ ፈረደ

(think) ፈረደ ; (form an opinion) ገመተ

judge (n.) ዳኛ

judgement ፍርድ ; (opinion) አስተያየት

judicial (system) የዳኝነት; (reform) የሕግ ; (mind) አመዛዛኝ

judiciary ሕግ፡ አውጪ

judicious (remark) ብልህ ; (person) አመዛዛኝ

jug ደምበጃን

juice ጭማቂ

July ሐምሌ

jumble, --- up አዘበራርቆ፡ አስቀመጠ

jump (v.) ዘለለ ; (give a sudden start) ደነበረ ; (rise suddenly) ተፍ፡ ብሎ፡ ተነሣ

(of heart) ገበሮ፡ መታ

jump in ዘሎ፡ ገባ

jump at ዘሎ፡ ወጣ

jump up ዘለለ

jump (n.) ዝላይ

junction መገናኛ

juncture መገናኘት

at this juncture እዚህ፡ ላይ

June ሰኔ

jungle ጫካ

junior የበታች;

(brother) ታናሽ

junk (n.) እንቶ፡ ፈንቶ ፤ ትርኪ፡ ምር

juridicial ሕጋዊ

jurisdiction ሥልጣን

jurisprudence ~~የሕግ፡ ዕውቀት~~ ሕግ፡ ፍልስፍና

jurist የሕግ፡ ዐዋቂ

just, ad. (man) ሐቀኛ ; (description) ትክክለኛ; (deserved) የሚገባ

just, adv. (exactly) ልክ ; (barely) ከንቲት

(a moment ago) ልክ፡ አሁን

(recently) ገና፡ አሁን; (only) ብቻ

justice ትክክለኛ፡ ፍርድ

Minister of Justice የፍርድ፡ ሚኒስትር፡

dispense justice ፈረደ

justification ምክንያት

justify ተገቢ፡ አስመሰለ ፤ ምክንያት፡ አቅርቦ፡ አቀረበ

jute ቃጫ

juvenile (delinquency) የወጣት፡ ልጆች ; (offender) የወጣት

juxtapose ጎን፡ ለጎን፡ አስቀመጠ

K

keen (mind) ንቁ ; (edge) ስለ

(interest) ከፍ፡ ያለ

keen edge ስለት

keep (vt.) ያዘ ; (retain) አስቀመጠ ; (guard) ጠበቀ;
(a secret) ቋጠረ ; (house) አስተዳደረ ; (temper) ገታ;
(honor) አከበረ
keep apart (vi.) ተገለለ
keep back ተከለከለ ፤ ወደ፡ ኋላ፡ መለሰ
keep from ከለከለ
keep in አቆየ
keep off (vi.) ገለል፡ አለ
keep out አስቀረ
keep up ያዘ
keeper ዘበኛ ፤ ጠባቂ
keeping (of a holiday) ማክበር;
(care, charge) ማኅደሪያ
be in keeping with ተስማማ ፤ ገጠመ
keepsake ማስታወሻ
kennel የውሻ፡ ቤት
kerchief ሻሽ
kernel ፍሬ
kerosene ጋዝ
kerosene lamp ኩራዝ
kettle ጀበና
key ቁልፍ ; (clue) ፍንጭ ;
(solution) ፍቻ
keyring ዘለበት

keystone መሠረት
kick ረገጠ
kick about ተዘዋወረ
kick around ወዲያ፡ ወዲህ፡ አለ፡
kid ግልገል ; (child) ሕፃን
kidnap አፍኖ፡ ወሰደ ;(a girl to marry her) ጠለፈ
kidney ኩላሊት
kill ገደለ ; (of a disease) ፈጀ
kilo ኪሎ፡
kilogram ኪሎ-ግራም
kilometer ኪሎ• ሜትር
kin ዘመድ
kind (n.) ዓይነት
kind, adj. (person) ደግ ;
(act)የደግነት
kindhearted ርኅሩኅ ፤ ደግ
kindle (vt.) አነደደ ; (anger) ቀሰቀሰ
kindle (vi.) ነደደ ; (eyes with joy) አበራ
kindly (adj.) የደግነት
kindly (adv.) በርኅራኄ
(very much) በጣም
kindness ደግነት
kindred (n.) ~~[illegible]~~ ዘመዶች
kindred (adj.) ~~ዘመዶች~~ በዝምድና፡ የተቀራረበ ፤ የተዘመደ

king ንጉሥ

become king ነገሠ

kingdom የንጉሥ፡ግዛት

kingly ንጉሣዊ

kinship ዝምድና

kiss (v.) ሳመ

kitchen ማብሰያ፡ቤት ፤ ወጥ፡ቤት

kite ወሳንሳ

kitten የድመት፡ግልገል

knead አቦካ

knee ጉልበት

drop on his knees ተንበረከከ

kneel ተንበረከከ

knife (v.) በጩቤ፡ወጋ

knife (n.) ቢላዋ ፤ ቢላ፡

knit ሠራ

knob እጀታ

knock (vt.) መታ

knock (vi.) በሩን፡አንኳኳ

(of engine) ሙኳ

knock down መቶ፡ጣለ ;(destroy) አፈረሰ

be knocked out በጣም፡ደከመ

knock-out መዘረር

knoll ጉብታ ፤ ትንሽ፡ኮረብታ

knot (v.) ቋጠረ

knot (n.) ቋጠሮ

make a knot ቋጠረ

knotty (board) ዓይን፡የበዛበት

(problem) በጣም፡አስቸጋሪ

know ዐወቀ ; (recognize) ለየ

knowingly ዐውቆ

knowledge ዕውቀት

come to one's knowledge ሰማ

knowledgeable ዐዋቂ

knuckle ዓዴቆ

L

label (n.) ምልክት

labor, v. (work) ሠራ ;

(exert effort) ጣረ

labor (n.) የሙያተኛ፡ዋጋ ፤

የጉልበት፡ዋጋ (effort) ጥረት ;

(process of giving birth to a child) ምጥ

laboratory ቤተ፡ሙከራ

laborer ሠራተኛ

labor pains የምጥ፡ሕመም

lack (v.) ጎደለ ፤ አጣ

lack (n.) እጥረት ፤ እጦት

lacking, be --- ጎደለ ፤ አጣ

ladder መሰላል

ladle (v.), --- out ጨለፈ

ladle (n.) ጭልፋ

lady ወይዘሮ ፤ ሴት፡ወይዘሮ

(wife) ባለቤት

ladies ሽሎሎች

lady of the house ባለቤት

lag ወደ፡ ኋላ፡ ቀረ

lake ሐይቅ:

lamb የበግ፡ ጠቦት

lame አንካሳ; (leg) ሽባ

lament (v.) አለቀሰ;

(regret) አዘነ

lament (n.) የሐዘን፡ እንጉርጉሮ

lamentable በጣም፡ የሚያሳዝን

lamentation ለቅሶ ፤ ልቅሶ

lamp ፋኖስ ፤ መብራት

lance ጦር

land (vt.) አሳረፈ

land (vi.) አረፈ ; (of passengers) ከመርከብ፡ ወረደ

land (n.) ምድር ፤ አገር

(soil) መሬት ; (dry land) የብስ

landholder ባለመሬት

landing (for ship) ማቆሚያ

landlady ባለቤት

landlord ~~[illegible]~~ የቤት፡ ጌታ:

landmark ምልክት ; (important event) ታሪክ፡ ምዕራፍ

landowner ባለርስት

land tenure የመሬት፡ ይዞታ:

lane የእግር፡ መንገድ ፤ ጠባብ፡ መንገድ.

language ቋንቋ.

languish (in prison) ማቀቀ ;

(roses)' ጠወለገ

lantern ፋኖስ

lap (v.) ገረፈ

lap (n.) ጭን

lapse, v. (fall into disuse) ተረሳ;

(end) አለቀ

larceny ሌብነት

large (house) ሰፊ. ; (man) ግዙፍ;

(big) ብዙ:

largely በጠቅላላው

larynx ማንቁርት

lash (v.) ገረፈ ; (the tail) ቆላ:

(of wind lashing the trees) መታ

lash (n.) ጅራፍ

last (v.) ቆየ ፤ በረከተ ፤ ፈጀ

last, adj. (coming after others) የመጨረሻ ; (directly before the present) ያለፈ

last (adv.) ከሁሉ፡ መጨረሻ ፤ በመጨረሻ

at last በመጨረሻ

lasting ዘላቂ ፤ የዘለዓለም

lastly በመጨረሻ

late (adj.) የመጨረሻ ;

(no longer living) ሟች

late (adv.) ዘግይቶ

be late (morning) አርፍዶ፡ መጣ;

(afternoon, evening) ዘግይቶ፡ መጣ

lately በቅርቡ፤ ከቅርብ፡ ጊዜ፡ ወዲህ

latent የተዳፈነ

later (adv.) ኋላ

later on በኋላ፤ ከዚያ፡ በኋላ

latest በቅርቡ፡ የወጣ፤ የመጨረሻ

latest news ትኩስ፡ ወሬ

at the latest ቢዘገይ ፡ ቢዘገይ፡

lather (n.) የሳሙና፡ አረፋ፡

latitude (in relation to equator) ኬክሮስ ; (freedom of judgement) የሐሳብ፡ ነጻነት፡

latrine ሽንት፡ ቤት

laud አመሰገነ

laugh ሣቀ

laughable አሣቂኝ

laughter ሣቅ፡

launch (a business) ከፈተ ; (an attack) ጀመረ ; (a spear) ወረወረ ; (missiles) ተኰሰ

laundry (clothes) የታጠበ፡ ልብስ; (place) የልብስ፡ ንጽሕና፡ መስጫ

lavish (adj.) አባካኝ

law ሕግ ; (practice of law) የጥብቅና፡ ሥራ ; (rules) ደንብ

practice law በሕግ፡ ሥራ፡ ተሰማራ

law court ፍርድ፡ ቤት

lawful ሕጋዊ

law-giver ሕግ፡ አውጪ

lawless (country) ሕግ፡ የለሽ; (person) ሕግ፡ የሚጥስ

lawn የግቢ፡ መስክ

lawsuit ሙግት

lawyer (attorney) ጠበቃ ; (trained in law) የሕግ፡ ዐዋቂ

lax (in work) ግድ፡ የለሽ; (not strict) ልል

lay (v.) አስቀመጠ ; (eggs) ጣለች; (plans) አወጣ ; (bandages) አሰረ ; (rug) አነጠፈ

lay aside ቈጠበ ; (abandon) ተወ

lay down (to sleep) አስተኛ ; (rules) አወጣ ; (arms) ~~[illegible]~~ አስረከበ

lay off ቀነሰ

lay open አጋለጠ

lay out (money) አወጣ

lay (adj.) የተራ ፡ሰው

layer (of sand) ደለል ; (of paper) ተደራቢ

layman (not an expert) ተራ፡ ሰው; (not a clergyman) መሀይምን

laziness ስንፍና

lazy ሰነፍ ; (slow moving) ዝግተኛ

lead (v.) መራ፤ አዝማች፡ ነበረ;

(guide by the hand) ሳበ;

(start) ከፈተ

lead (n, rhymes with 'bead')

ቀዳሚነት ; (clue) ፍንጭ

take the lead ቀደመ፤ ቀዳሚነት፡ ያዘ

lead (n., rhymes with 'dead')

እርሳስ

leader መሪ

leadership መሪነት

leading (thought) ዋና ;

(scientist) የታወቀ

leading article ርእስ፡ አንቀጽ

leaf ቅጠል

leaflet ጽሑፍ

league ማኅበር

League of Nations የዓለም፡ መንግሥታት፡ ማኅበር

leak, v. (pot) አፈሰሰ ; (ship) ውሃ፡ አስገባ ; (tire) ተነፈሰ

leak out (water) ተንጠባጠበ

(story) ተሰራጨ

leak (n.) ቀዳዳ ፤ የሚያፈስ፡ ቀዳዳ

lean, v. (slant) ዘመመ ; (rest against) ተደገፈ ; (be inclined) አዘነበለ

lean backwards ወደ፡ ኋላ፡ ደገፍ፡ አለ

lean forward አንገቱን፡ ሰቅ፡ አደረገ

lean on ተደገፈ

lean out ተንጠለጠለ

lean (adj.) ቀጭን፡

leap (v.) ዘለለ ; (to conclusions) ቸኮለ

leap (n.) ዝላይ

leap year ዘመነ፡ ዮሐንስ

learn ተማረ ; (become informed) ዐወቀ ; (hear) ሰማ

learn by heart በቃል፡ ያዘ

learned የተማረ

learner ተማሪ

learning ትምህርት;

(knowledge) ዐዋቂነት

lease (v.) ተከራየ ፤ ተኰናተረ

lease (n.) ኮንትራት

leash (n.) ማሰሪያ

hold in leash (temper) ገታ

least, at --- ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፤ ያህል

~~who~~ not is the least በፍጹም

the least ቀላል ፤ ከሁሉ፡ አነስተኛ

not the least ፈጽሞ

leather ቆዳ

leave (vt.) ተወ ; (a job) ለቀቀ ; (home) ተለየ ; (go out) ወጣ

(hand over) ጣለ ; (bequeath) ተናዞ፡ ሞተ ፤ አወረሰ

leave (vi.) ሄደ ; (train) ተነሣ

leave alone ተወ

leave out ተወ ፤ ገደፈ

leave, n. (permission) ፈቃድ ; (period of time of permission) ስንብት

take leave ተሰናበተ

lecture ንግግር

deliver (give) a lecture ንግግር ፡ አደረገ

lecturer ተናጋሪ

leech አለቅት ~~[illegible]~~

lees አተላ

left ግራ

left-handed ግራኝ

leftover ትራፊ

leftovers የተረፈ ፡ ምግብ

leg እግር

legacy ውርስ

legal ሕግ ፡ የተከተለ

(advisor) የሕግ

legalize ሕጋዊ ፡ አደረገ

legation ሌጋሲዮን

legend አፈ ፡ ታሪክ

(inscription) ጽሑፍ

legion ክፍለ ፡ ጦር

legislate ሕግ ፡ አወጣ

legislation ሕግ ; (enacting of laws) ሕግ ፡ ማውጣት

legislative የሕግ

legislative decree ድንጋጌ

legislature የሕግ ፡ አውጪ ፡ ጉባኤ

legitimate ሕጋዊ ; (born in wedlock) በሕግ ፡ ጋብቻ ፡ የተገኘ ; (reasonable) በቂ

leisure ትርፍ ፡ ጊዜ

lemon ሎሚ

lend (money) አበደረ ; (objects) አዋሰ

length ርዝመት

at length በሰፊው

lengthen አረዘመ

lengthy ረዥም ፤ ረጅም

lenient ልል

Lent የሁዳዴ ፡ ጾም

lentil ምስር

leopard ነብር

leper ቆማጣ

leprosy ቁምጥና

less (adj.) ያነሰ

less (adv.) ያነሰ ፤ ጥቂት

be less አነሰ

lessen ቀነሰ ፤ አሳነሰ

lesson ትምህርት

give lessons አስተማረ

let (lease) አከራየ ; (permit) ፈቀደ

let by አሳለፈ

let down አወረደ

let in አስገባ

let off አወረደ ; (allow to go free) ለቀቀ

let out ለቀቀ ; (a secret) አወጣ

let up (storm) በረደ፡ አለ

(rain) ጋብ፡ አለ

letter ደብዳቤ ; (of alphabet) ፊደል

letters (literature) ሥነ፡ ጽሑፍ

letter box ፖስታ፡ ሣጥን

lettuce ሰላጣ

level (v.) አስተካከለ ;

(raze) አወደመ ; (aim) ሰነዘረ

level off ደለደለ

level (n.) ደረጃ ; (story) ፎቅ

level (adj.) ደልዳላ ; (voice) ያልተለዋወጠ

be level ተስተካከለ

lexicon መዝገበ፡ ቃላት

liability ወመረያ፡ ኪሣራ ;

(hindrance) መሰናክል ;

(responsibility) ኃላፊነት

liable, be --- to ሳ + negative imperfect + አይቀርም

(he is liable to forget ሳይረሳ፡ አይቀርም)

liar ውሸታም

liberal (generous) ለጋስ ;

(tolerant) የማይቃረን ;

(donation) በርከት፡ ያለ

liberate ነጻ፡ አወጣ

liberty ነጻነት ; (privilege) መብት

be at liberty ቻለ ; (not confined) እስር፡ ቤት፡ አይደለም

librarian ዐቃቤ፡ መጻሕፍት

library ቤተ፡ መጻሕፍት

license (permission) ፈቃድ ;

(lawless behavior) ብልሹ፡ ምግባር

license plate ሰሌዳ

lick ላሰ ; (flame licking the roof) ገረፈ

lick~~ing~~ up ጠቃጋ፡ መመረከ

lid መክደኛ ፣ ክዳን

(of pot) እሌሶ

lie (lied) ዋሸ

lie (n.) ውሸት

lie, lay (be situated, exist) ተገኘ ፣ ነው ; (be in a resting position) ተጋደመ

lie back ተንጋለለ

lie down ጋደም፡ አለ

lieutenant መቶ፡ አለቃ

life ሕይወት ; (a living person) ሰው ; (biography) የሕይወት፡ ታሪክ፡

(movement, animation) እንቅስቃሴ ; (cheering influence) ድምቀት ; (way of life) ኑሮ

come to life ነፍስ፡ዘራ

for life ዕድሜ· ልኩን

→ lose one's life ሞተ

→ take (one's) life) ራሱን፡ ገደለ

way of life አኗኗር

life belt የመንሳፈፊያ፡ ቶጃቁ·

life imprisonment ዕድሜ፡ ይፍታህ

life insurance የሕይወት· ዋስትና· ዋጋ

lifetime ዕድሜ

lift (v.) አነሣ ; (the voice) ከፍ፡ አደረገ ; (the spirit) ~~አነቃ~~ አነቃቃ

be lifted (boycott) አበቃ ; (restrictions) ተሰረዘ

lift up ቀና፡ አደረገ

lift (n.) አሳንሰር

light (vt.) አበራ ; (pipe) ለኮሰ ; (fire) አያያዘ ; (match) ~~ጫ~~ ጫረ

light, vi. (wood) ተቀጣጠለ

(come to rest) አረፈ ; (get down) ወረደ ~~(of a bird) ወፍ~~ ~~ወፍ~~

be lit ተያያዘ

light (n.) ብርሃን ; (lamp) መብራት ; (traffic light) የትራፊክ፡ መብራት ; (match) ክብሪት ; (enlightenment) ማብራሪያ

bring to light አስገኘ

come to light ተገኘ

put on the light መብራቱን፡ አበራ

put out the light መብራቱን፡ አጠፋ

light, adj. (coat) ስስ ; (food) ቀለል፡ ያለ ; (sentence) አነስ፡ ያለ ; (color) ብሩህ

lighten, vt. (load) ቀነሰ ; (problem) አቃለለ

lighten, vi. (sky) ጠራ ; (face) ፈገግ፡ አለ ; (flash lightning) ተብለጨለጨ

light-footed ቀልጣፋ

light-headed የማይረጋ

light-hearted ግድ፡ የሌለው

lighting ብርሃን

lightning መብረቅ

like (vt.) ወደደ ፤ ፈለገ

like (prep.) እንደ

be like መሰለ

likely (probable) የሚቻል:

(suitable) ምቹ

liken መሰለ

likeness መመሳሰል

likewise እንደዚሁ

liking, have a --- for ወደደ

limb እጅ፡ እግር;

(branch) ቅርንጫፍ

limber (v.) አፍታታ

limber, adj. (flexible) የሚገለመጥ;

(nimble) የቀለጠፈ

lime (citrus fruit) ሎሚ ;

(chemical compound) ኖራ

limit (v.) ወሰነ

limit (n.) ልክ

limits ክልል

within the limit በመጠን

limited (adj.) የተወሰነ

limp (v.) አነከሰ

limp (adj.), be --- (collar) ተኰሸ

go limp ተዝለፈለፈ

look limp (flower) ጠወለገ

limpid የጠራ

line (v.) አሠመረ

be lined (face) ተጨማደደ

lineup አሰለፈ

line (n.) መሥመር; (telephone) የስልክ፡ መሥመር;

(row) ሰልፍ ; (descendence) ዘር ; (in poetry) ሐረግ ;

(frontier) ድንበር ; (of fisherman) የዓሣ፡ ማጥመጃ

(clothes line) ሽቦ ;

(letter) ደብዳቤ ; (range of items) ዓይነት፡ እቃ ;

(business) ሥራ ; (plan of thought) መልክ

bring into line በመሥመር፡ አስገባ

form a line ተሰለፈ

in line with በ··· መሠረት

keep in line ገታ

lineage ዘር

linen (cloth) ሊኖ ; (of bed) የአልጋ፡ ልብስ፡

liner ትልቅ፡ መርከብ

linger, --- about ወደ፡ ወዲህ፡ አለ

lining ገበር

link (v.) አያያዘ

link (n.) ማያያዣ

linseed ተልባ

lion አንበሳ

lip ከንፈር; (of cup) አፍ

liquefy አቀለጠ

liquid (n.) ፈሳሽ፡ ነገር

liquid (adj.) ፈሳሽ

liquor አልኮል

lisp ተኮላተፈ

list (v.) በዝርዝር፡ ጻፈ ፤ በዝርዝር፡ አኖረ ፤ መዘገበ

list (n.) ዝርዝር

listen አዳመጠ፤ ሰማ

liter ሊትር

literacy መጻፍና ማንበብ

literally ቃል፡ በቃል

literate የተማረ፡

literature ሥነ፡ ጽሑፍ

litigate ተሟገተ

litigation ሙግት

litter (v.) አቆሸሸ ; (strew about) በተተነ

litter, n. (scraps scattered about) ቆሻሻ ; (cot) ቃሬዛ ; (young born at one time) ግልገሎች

little ጥቂት ; (small) ትንሽ; (unimportant) የማይረባ ; (voice) ዝቅ፡ ያለ

a little ትንሽ፡ ትንሽ

little by little ቀስ፡በቀስ

liturgy የቤተ፡ክርስቲያን፡ ሥነ፡ ሥርዓት

live (v.) ኖረ ; (maintain oneself) ተዳደረ ; (remain in memory) ተቀርጾ፡ ኖረ

live (adj.) ነፍስ፡ ያለው ; (full of life) ታታሪ

livelihood መተዳደሪያ

lively ንቁ ; (color) ደማቅ; (time) ሞቅ፡ ያለ ; (interest) ከፍ፡ ያለ

liven አደመቀ

liven up ነቃ፤ ነቃ፡ አለ

liver ጉበት

livestock ከብቶች

living (n.) ኑሮ

make a living ተዳደረ

living በሕይወት፡ ያለ ; (language) የሚሠራበት;(tree) ለምለም

living conditions የኑሮ፡ ሁኔታ

living costs የኑሮ፡ ውድነት

living room ሳሎን፡

lizard እንሽላሊት

load (vt.) ጫነ ; (stomach with food) ጎረሰ ; (gun) አጎረሰ

load (n.) ሸክም፤ ጭነት

loaf of bread ዳቦ

loafer ሥራ፡ ፈት

loan, v. (money) አበደረ

(object) አዋስ

loan, n. (money) ብድር፤ የገንዘብ፡ብድ

(object) መዋስ

loanword የተወሰደ፡ ቃል

loathe በጣም፡ ጠላ፡

lobby መተላለፊያ

local የሀገር፡ ውስጥ፤ ያገር; (train) በየጣቢያው፡ የሚቆም; (injury) ባንድ፡ ቦታ፡ ላይ፡ የሆነ

locality ቀበሌ

locate (find) ፈልጎ፡ አገኘ ፤ ደረሰ(በት); (determine the position) አመለከተ ; (establish) አቋቋመ

location አቀማመጥ

lock (v.) ቆለፈ

be locked out ተዘጋ(በት) ፤ በሩ፡ ተዘጋጋበት ፣ ውጭ፡ አደረ

lock up ቆለፈ(በት)

lock (n.) የቁልፍ፡ እንጓ;

(of hair) ዘለላ፡

lock, stock and barrel እንዳለ

locker ሣጥን

locksmith ቁልፍ፡ ሠራተኛ

locomotive ባቡር

locust አንበጣ

lodge (vt.) አኖረ ; (a complaint) አቀረበ

lodge (vi.) ሰነበተ ; (of a bullet in the shoulder) ገብቶ፡ ቀረ

lodge (n.) የማረፊያ፡ ጎጆ;

(local branch) የማኅበር፡ ቅርንጫፍ

lodger ተከራይ

lodgings መኖሪያ

loft ቆጥ

lofty ከፍተኛ ; (manner) ኮራ፡ ያለ

log, v. (fell and remove timber) መነጠረ ; (enter in the record book) በማስታወሻ፡ ደብተር፡ ጻፈ

log, n. (trunk of tree) ግንድ ;

(record book) ማስታወሻ፡ ደብተር

logic (sound reasoning) ምርምር;

(way of reasoning) አስተሳሰብ፡

(science) ሎጂክ

loin ወገብ

loiter ተንቀዋለለ

lone ብቸኛ

loneliness ብቸኝነት

lonely (life) የብቸኝነት ;

(road) ጭር፡ ያለ

lonesome ብቸኛ

be lonesome for ናፈቀ

feel lonesome ብቸኝነት፡ ተሰማው

long (v.) ጓጓ

long (adj.) ረጅም ፤ ረዘም፡ ያለ

long (adv.) ብዙ ፤ ብዙ፡ ጊዜ

long ago ከብዙ፡ ጊዜ፡ በፊት፡

a long time ብዙ፡ጊዜ

a long time ago ከብዙ፡ ጊዜ፡ በፊት

all day long ቀኑን፡ ሙሉ፡

longanimity ታጋሽነት

longing ጉጉት ፤ ናፍቆት

longitude ኬንትሮስ

look (v.) ተመለከተ ; (appear) መሰለ

look after (watch) ጠበቀ ;

(follow with the eyes) በዓይን፡ ተከተለ

look alike ተመሳሰለ

look around ዞሮ፡ ፈለገ

look at አየ ; (examine) መረመረ

look back ዞር፡ አለ

look for ፈለገ

look good አማረ

look into መረመረ

look like መሰለ

look out ተመለከተ ፤ ወደ፡ ውጭ፡ አየ

look through (search) ፈተሸ ; (with the eyes) በውስጡ፡ አየ

look up ቀና፡ አለ

look (n.) መልክ

give (one) a look ተመለከተ

have a look አየ

loom የሸማኔ፡ እቃ

loophole (opening) ቀዳዳ ; (basis for evasion) ማምለጫ፡ መንገድ

loose (adj.) ልል ; (conduct) ልክስክስ ; (translation) በጣም፡ የማይቀርብ

be loose ላላ

cut loose ቆረጠ

get loose አመለጠ ፤ ጠፋ

let loose ለቀቀ

turn loose ፈታ፡ ለቀቀ

loosen (vt.) አላላ; (soil) አለሰለሰ

loosen (vi.) ~~አለሰለሰ~~ ላላ

loot (v.) ዘረፈ

loot (n.) ምርኮ ፤ የዘረፈው

loquacious ለፍላፊ፡

lord ፈላጭ፡ ቆራጭ ; (official) ሹም

lorry የጭነት፡ መኪና፡

lose ጣለ ፤ ጠፋ(በት);

(the way) ሳተ ; (game) ተሸነፈ; (lawsuit) ተረታ ; (a leg) ተቆረጠ ; (waste) አጠፋ

be lost ጠፋ ; (spoiled) ተበላሸ; (in thought) ተዋጠ

lose the edge ዶለዘ

lose the fight ተሸነፈ

lose one's hair ተመለጠ ፤ በራ፡ ሆነ፡

lose money ከሰረ

loss ጉዳት ፤ ማጣት

(of a person) ሞት ; (of hair) መመለጥ;(in business) ኪሳራ

be at a loss ግራ፡ ገባ(ው)

lost (adj.) የጠፋ ; (time) የባከነ ; (battle) ድል፡ የሆነበት

lot (piece of ground) መሬት ; (chance) ዕድል ; (package) ጥቅል

lots of ብዙ

a lot በጣም፡

quite a lot ብዙ ; (time) ብዙ፡ ጊዜ

draw lots ዕጣ ፡ አወጣ

loud (voice) ጎልህ ፡ ከፍ ፡ ያለ;

(laughter) ጮኽ ፡ ያለ ; (person) የሚንጫጫ ; (color) ደማቅ

loudspeaker የድምፅ ፡ ማጉሊያ

louse ቅማል

love (v.) ወደደ

love (n.) ፍቅር ; (of books) መውደድ

fall in love ፍቅር ፡ ያዘው

lovely ደስ ፡ የሚል ፤ አስደሳች

lover ፍቅረኛ ፤ ወዳጅ

low, adj. (voice) ዝቅ ፡ ያለ ፤ ቀለስተኛ;

(work, position) ዝቅተኛ;

(number) አነስ ፡ ያለ

low (adv.) ዝቅ ፡ ብሎ

be low ዝቅ ፡ አለ

low country ቆላ

lower (v.) ዝቅ ፡ አደረገ;

(make less) ቀነሰ

lower (adj.) የበታች

lowland ቆላ:

lowly ከተራ ፡ የተወለደ;

(occupation) ወራዳ:

loyal ታማኝ

loyalty ታማኝነት

lucid (lake) የጠራ ; (explanation) ግልጽ

luck ዕድል ፤ ገድ

good luck! ይቅናህ

lucky ዕድለኛ

lucrative ትርፍ ፡ ያስገኝ

luggage ጓዝ

lukewarm ለብ ፡ ያለ ; (reception) ቀዝቃዛ:

lullaby እሹሩሩ

lumber ሳንቃ

luminous ብርሃን ፡ የበዛበት;

(report) ግልጽ

lump, vt. (put together) አጠቃለለ

lump, vi. (form into a lump) ጓጎለ

lump, n. (of sugar) ጓል ፤ እንጓር;

(swelling) እብጠት

lump sum ባንድ ፤ በጠቅላላው

lunatic እብድ

lunch (v.) ምሳ ፡ በላ

lunch (n.) ምሳ

lung ሳምባ ፤ ሳንባ

lure (n.) ማራኪነት

lurk አደፈጠ ፤ እያደባ ፡ ሄደ

lush ለምለም

lust (for power) ከፍተኛ ፡ ጉጉት:

luster (of pearls) ማንጸባረቅ;

(of eyes) ድምቀት

luxurious ምቾትና ፡ ውበት ፡ ያለው:

luxury ድሎት ፤ ምቾት

lyre ክራር

M

machine መኪና

mad እብድ ; (efforts) ከንቱ

be mad ጦፈ

be mad at ተናደደ

madam ወይዘሮ

madden (cause to become insane) አሳበደ ; (enrage) አናደደ

mademoiselle ወይዘሪት

madness እብደት

magazine (storehouse) መጋዘን; (publication) መጽሔት

magic (n.) አስማት ፤ መተት; (beauty) ውበት

magician አስማተኛ ፤ ጠንቋይ

magnanimity ለጋስነት

magnanimous (generous in forgiving) ይቅር፡ ባይ;(Kind)ደግ ቸር

magnet ማግኔት

magnificent ዕጹብ፡ ድንቅ

magnify አጉልቶ፡ አሳየ; (exaggerate) አጋነነ

magnifying glass የሚያጎላ፡ መነጽር

magnitude (size) መጠን; (importance) ከፍተኛነት

maid ገረድ

maiden ልጃገረድ

mail (v.) በፖስታ፡ ላከ

mail (n.) ደብዳቤ

mailbox የፖስታ፡ ማጠራቀሚያ፡ ሣጥን

mailman ፖስተኛ

main (n.), in the --- አብዛኛው፡ ጊዜ ፤ በጠቅላላው፡

main (adj.) ዋና

mainly አብዛኛውን፡ ጊዜ

maintain (family) አስተዳደረ; (equipment) ያዘ ; (a road) በሚገባ፡ ጠበቀ;(security) አስከበረ

maize በቆሎ፡

majestic ባለግርማ

majesty ግርማ

Majesty, His --- ግርማዊነታቸው፡

Your Majesty! ግርማዊ፡ ሆይ

major (n.) ሻለቃ

major (adj.) ዋና ; (problem) ከባ፡ ጸክ; (war) ታላቅ

majority አብዛኞቹ ; (through vote) የድምፅ፡ ብልጫ; (legal age of responsibility of man) ዓቅመ፡ አዳም ; (of woman) ዓቅመ፡ ሔዋን

make አደረገ ፤ ሠራ ; (meal) አዘጋጀ; (the bed) አነጠፈ ; (earn) አገኘ; (friends) አፈራ

make off ሸሽቶ፡ ሄደ

make out (understand) ገባ(ው); (see clearly) ለየ ; (fill out) ሞላ
make up (invent) ፈጠረ ; (a sentence) ሠራ ; (a prescription) አዘጋጀ
make up with ታረቀ
make (n.) ዓይነት
malady በሽታ
malaria ወባ
practice, n. (habit) ልማድ ;
(repeated performance) ልምምድ ;
(actual use of something) ግብር ;
(of a doctor) ሥራ
be in practice በሥራ፡ ላይ፡ ዋለ

practiced (adj.) ሠልጡን

prairie የሣር፡ ሜዳ

praise, v. (glorify) አመሰገነ;
(speak favorably of) አደነቀ

praise (n.) ምስጋና

pray (vt.) ለመነ
pray (vi.) ጸለየ

prayer ጸሎት
offer prayers ጸሎት፡ አደረገ

preach ሰበከ

preacher ሰባኪ

precaution ጥንቃቄ;
(warning) ማስጠንቀቂያ
take precautions ተጠነቀቀ

precede (happen before in time) ቀደመ ; (be before in rank) በለጠ ; (be before in place) ፊት፡ ፊት፡ ነበረ

precedence ቅድሚያ
take precedence ቅድምናት፡ አለው፤ ቀደመ

preceding ቀዳሚ፤ ያለፈ

precept (rule of conduct) ምግባር;
(maxim) ምሳሌ

precinct ቀበሌ
precincts ቅጽር፡ ግቢ ; (of town) ክልል

precious (costly) የከበረ ;
(highly valued) ጠቃሚ ;
(loved) የሚወደድ; (refined) ረቂቅ

precipice ገደል

precipitate (bring about) አስከተለ; (hurl down) አንከባለለ

precipitation (haste) ችኮላ;
(rain) ዝናብ

precise (careful) ጠንቃቃ ;
(strict) ጥብቅ ; (accurate) ትክክለኛ
at the precise moment ልክ

precisely (exactly) ልክ ;
(accurately) በትክክል

precision ትክክለኛነት

precursor ቀዳሚ

predecessor በፊት፡ በቦታው፡ የነበረ፤ [illegible]

predestined የተወሰነ፤ ከመጀመሪያው፡ የታደለ

predetermine አስቀድሞ፡ ወሰነ

predicate (n.) አንቀጽ

predict ተነበየ

prediction ትንቢት

predilection መውደድ

have a predilection ወደደ

predominant (prevailing)

በ[illegible]ተበላጭ፡ የሚታይ;

(greater in power) የበለጠ

preeminent, be --- ላቀ

preface (n.) መቅድም

prefer መረጠ ; (like) ፈለገ

preference, have --- for ~~[illegible]~~ መረጠ

give preference አደላ

pregnant ነፍሰ፡ ጡር;

(animal) ከባድ

become pregnant ፀነሰች

premature ጊዜው፡ ያልደረሰ

Premier ጠቅላይ፡ ሚኒስትር

premises ግቢ

premium, n. (price) ትርፍ;

(payment) ክፍያ

premium (adj.) ከፍተኛ

preparation ዝግጅት

be in preparation ተዘጋጀ

prepare አዘጋጀ ; (meal) ሠራ ;

(a medicine) ቀመመ

preponderant ከሁሉ፡ የበለጠ

prescribe አዘዘ

be prescribed (of duties)

ተወሰነ ; (of textbooks)

ተመደበ

prescription የመድኃኒት፡ ማዘዣ፤

የሐኪም፡ ትእዛዝ

presence መኖር

present, v. (submit) አቀረበ ; ‡

(give as a gift) ሸለመ ;

(a drama) አሳየ ; (introduce)

አስተዋወቀ ; (difficulties)

አመጣ

present, n. (gift) ስጦታ ;

(present tense) ያሁን፡ ጊዜ

at present አሁን

present (adj.) ያሁኑ

present! (in school) አቤት

be present ነበረ (in the past), አለ

← (in the present) ~~[illegible]~~

presently (now) አሁን ; (soon)

በቅርብ

present tense ያሁን፡ ጊዜ

preservation መጠበቅ

preserve (v.) ጠበቀ

preserve, n. (tract of land where

animals are protected) የዱር፡

አራዊት፡ ክልል

preserves የቆርቆሮ፡ ምግብ

preside, --- over (act as chairman)

በሊቀ፡ መንበርነት፡ መራ;

(have control over) ተቆጣጠረ

President ፕሬዚዳንት

press, vt. (iron) ተኮሰ ; (clasp) ← ጨበጠ ; (a button) ጫን፡ አለ; (squeeze out) ጨምቆ፡ አወጣ ; (the trigger) ሳበ ; (hug) ← አቅፎ፡ አደረገ ; (urge) ← አጥብቆ፡ ጠየቀ; (push) ገፋ

press down ጫን፡ አለ

press, n. (printing) የማተሚያ፡ መኪና; (machine to crush) መጭመቂያ ← መኪና ; (newspaper) ጋዜጠኞች

go to press ታተመ

pressing (urgent) አስቸኳይ ; (important) ብርቱ

pressure (stress) ጭንቀት ; (of air) ያየር፡ ግፊት ; (insistence) መገፋፋት

bring pressure on አስገደደ

prestige ክብር

prestigious ስመ፡ ጥር

presumably ምናልባት

presumed የሚባል

presumptuous ደፋር

pretend በሐሰት፡ አለ፤ አስመሰለ

pretense (excuse) ሰበብ ; (false display) ለይምሰል

pretext ሰበብ ፤ ምክንያት

pretty (adj.) ቆንጆ ; (moderately large) በርከት፡ ያለ

pretty (adv.) በጣም

prevail (win) ተሳካ ; (predominate) አየለ ; (persist) አሁንም፡ አለ

prevalence ብዛት

prevalent, be --- በብዛት፡ ተገኘ፤ አየለ

prevent ከለከለ፤ አገደ

preventive (n.) መከላከያ

previous የፊተኛው፤ ቀደም፡ ያለ

previously ከዚህ፡ በፊት

price (n.) ዋጋ ; (what must be paid to obtain a thing) መሥዋዕት

priceless እጅግ፡ ውድ

prick (with needle) ወጋ ; (with claws) ቧጠጠ

prickle (n.) ጥቃቅን፡ እሾህ

prickly እሾሀማ

pride ኩራት ; (person giving others satisfaction) መኩሪያ

priest ቄስ

priesthood ክህነት

priestly የቄስና

primarily (above all) በይበልጥ ; (principally) በመሠረቱ

primary (original) መሠረታዊ ; (chief) ዋና

primary school አንደኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤት

prime (n.) ጎፈሳ

prime of life የዕድሜ፡ ጎፈሳ

prime (adj.) ዋና

prime minister ጠቅላይ፡ ሚኒስትር

primer ዐወደ፡ ንባብ

primitive (of early days) የጥንት;

(simple and crude) ወደ፡ ኋላ፡ የቀረ;

(uncivilized) ያልሠለጠነ

prince ልዑል

Crown Prince አልጋ፡ ወራሽ

princess ልዕልት

principal, n. (head of school) ዲሬክተር ; (sum of money) ዋና፡ ገንዘብ

principal (adj.) ዋና

principle (rule of science) መሠረታዊ፡ ደንብ;

(basic facts) መሠረተ፡ ሐሳብ;

(rule of conduct) ደንብ፤ ሥርዓት;

(fundamental belief) እምነት፤ የሚያምንበት፡ ነገር

as a matter of principle በሕግ፡ መሠረት

print (v.) አተመ ; (write in letters that resemble those made by type) በእስሀ፡ ጻፈ

print (n.) ፊደሎች ; (copy of picture) ቅጂ ; (imprint) አሻራ

be in print ይገኛል

be out of print አለቀ

printer አታሚ

printing እትም

printing press ማተሚያ፡ ቤት

priority ቀዳሚነት

prison እስር፡ ቤት

prisoner እስረኛ

take prisoner ማረከ

privacy (seclusion) ለብቻ፡ መሆን

(secrecy) ጭምት

private (n.) ተራ፡ ወታደር

private (adj.) የግል ; (having no public office) ተራ

in private ለብቻ

private secretary ልዩ፡ ጸሐፊ

privation ችግር

privilege ልዩ፡ መብት

prize, n. (reward) ሽልማት;

(something very valuable) የሚበልጥ

probability ይሆናል

probable, be --- ሳ + negative imperfect + አይቀርም

probably ምናልባት

probe (v.) መረመረ

probe (n.) ምርመራ

problem (question proposed for

discussion) ጉዳይ ; (difficult issue) ችግር ; (in mathematics) ጥያቄ

procedure ሥርዓት

proceed ቀጠለ ; (on a trip) ጉዞ፡ ቀጠለ

proceeding ነገር

proceedings የሥራ፡ ውጤት

process (n.) ጉዳይ ; (set of actions) ዘዴ

procession ሰልፍ

proclaim ዐወጀ ; (announce, make known) አስታወቀ፤ ገለጸ

proclamation ዐዋጅ

procure አገኘ

prod, v. (poke) ወጋ ወጋ፡ አደረገ; (urge on) ገፋፋ

prod (n.) ሹል፡ ዘንግ

prodigious የሚያስደንቅ

produce, v. (make) ሠራ ; (bring forth crops) አበቀለ ; (bring forward) አቀረበ ; (show) አሳየ ; (bring about) አስገኘ

product ሀብት፤ እቃ; (of farm) ምርት

production (producing) መሥራት; (what is produced) የፋብሪካ፡ ውጤት

productive (activity) ጠቃሚ ; (business) ትርፍ፡ ያስገኛ; (soil) ለም ; (writer) ብዙ፡ መጻሕፍት፡ የሚጽፍ

profane (v.) አረከሰ

profane, adj. (literature) ዓለማዊ; (language) የብልግና

profess (declare) ገለጸ ; (practice as a religion) አመነ; (pretend) አሰ

profession (occupation) ሙያ ; (group of people engaged in an activity) ዓለም

professional, adj. (having to do with a profession) የሙያ ; (not amateur) ፕሮፌሽናል

professor መምህር፤ ፕሮፌሰር

proficiency ችሎታ

proficient ብቁ፡ ችሎታ፡ ያለው

profile ጐን

profit, n. (advantage) ጥቅም ; (in business) ትርፍ
make a profit አተረፈ

profitable (business) ትርፍ፡ የሚያስገኝ ; (beneficial) ጠቃሚ

profound (learning) ጥልቅ ; (scholar) ጥልቅ፡ ዕውቀት፡ ያለው; (silence) ፍጹም; (grief) ከባድ

profuse በጣም፡ ብዙ

profusely ከመጠን፡ በላይ

progenitor ቅድመ፡ አያት;
(originator) አመንጪ

progeny ተወላጆች

prognosis ግምት ፤ አስተያየት

program ፕሮግራም

progress, v. (develop) ተገሠገሠ ፤ ተፋጠነ ; (improve) እየተሻሻለ፡ ሄደ

prohibit (forbid) ከለከለ;
(prevent) አስቀረ

project, v. (a beam of light) ፈነጠቀ ; (shells) አስፈነጠረ;
(plan) አቀደ

project (n.) እቅድ ፤ ውጥን

proliferate እየተባዛ፡ ሄደ

prolific ወላድ፡

prologue መቅድም

prolong አራዘመ

prolonged (adj.) የረጅም፡ ጊዜ

prominent (well-known) ስመ፡ ጥር;
(eyes) የፈጠጠ ; (hump) ጎላ፡ ያለ

promise (v.) ቃል፡ ገባ ; (give reason to expect) [illegible]

promise (n.) ቃል ፤ የገባው፡ ቃል

promising ተስፋ፡ ያለው ፤ ተስፋ፡ የሚጣልበት

promote (trade) አስፋፋ ; (a company) ለማቋቋም፡ ረዳ ;
(peace) አደረጀ
be promoted የደረጀ፡ እድገት = አገኘ

promotion ሹመት ፤ እድገት;
(of a campaign) ማስፋፋት

prompt, v. (cause to do something) ገፋፋ ; (inspire) አፈለቀ ;
(remind an actor of the words needed) ፍንጭ፡ ሰጠ

prompt, be --- ፈጠነ

promptly ልክ

promulgate ዐወጀ

pronounce (declare) አስታወቀ;
(utter the sounds) ተናገረ

pronunciation አባባል ፤ የቃላት፡ አነባበብ

proof ማስረጃ ፤ መረጃ
put to the proof ፈተነ

propaganda የሐሰት፡ ወሬ ፤ ፕሮፓጋንዳ

propagate አሰራጨ

proper (suitable) ተገቢ ; (diet) የተሟላ ; (authorities) አግባብ፡ ያለው

proper name የተጸውዖ፡ ስም

properly በደንብ

property ንብረት ፤ ሀብት;
(land) መሬት; (attribute) ጠባይ

prophecy ትንቢት

prophesy ተነበየ

prophet ነቢይ

propinquity ጉርብትና

propitious (of weather) ተስማሚ;

(of gods) ቸር

proportion (n.) ክፍል

proportions መጠን

in proportion to ከ···ጋር፡ ሲታይ

proportionate, be --- ተመጣጠነ

proposal ሐሳብ ; (of marriage)

ለጋብቻ፡ ያቀረበው፡ ጥያቄ

propose (suggest) ሐሳብ፡ አቀረበ;

(intend) አሰበ

proposition ሐሳብ

proprietor ባለቤት

propriety (proper behavior)

ሥነ፡ ሥርዓት

proscribe አወገዘ

prose ስድ፡ ንባብ

prosecute (continue) ቀጠለ;

(bring suit against)

ሕግ፡ ፊት፡ አቀረበ

prosecution (carrying on)

እንደዚ፤ ማከናወን ; (conducting of legal action) ክስ

prospect, n. (hope) ተስፋ ;

(chance) ዕድል ; (view)

ትዕይንት

prospective የወደፊት

prosper ~~[illegible]~~ በለጸገ

prosperity ብልጽግና

prosperous (city) የበለጸገ;

(business) የሚያብብ

prostitute ሴተኛ፡ አዳሪ

prostrate, v. (throw down)

ገነደደሰ ; (weaken)

አደከመ

prostrate oneself (before god)

ሰገደ; (before the conqueror)

በግንባሩ፡ ወደቀ

prostrate (adj.), fall --- ተዘረረ

protect (industry) ጠበቀ ; (the eyes) አዳነ ; (freedom)

ተከላከለ

protection መከላከያ

protector የሚከላከል

protest, v. (object) ተቃወመ;

(assert, maintain) ተከራከረ

protest (n.) ተቃውሞ ; (formal complaint) የተቃውሞ፡ መልእክት

Protestant ፕሮቴስታንት

protocol ፕሮቶኮል

protract አራዘመ

protrude አወጣ

proud ኩሩ

be proud ኮራ

prove (show that it is true)

አረጋገጠ ; (bring proof)

~~አስረዳ~~

አስረዳ ; (test the quality) መሰከረ

proverb ምሳሌ

provide (require) አዘዘ ; (give) ሰጠ ; (furnish) አዘጋጀ

provide for አስተዳደረ

be provided with አገኘ

providence አርቆ፡ አስተዋይነት

Providence እግዚአብሔር

province (division of a country) ጠቅላይ፡ ግዛት ; (proper work) ተግባር ; (authority) ሥልጣን

provincial (government) የጠቅላይ ግዛት ; (manners) የባላገርነት

provision (providing) ማቅረብ ; (stipulation) አንቀጽ፤ ደንብ ; (plan made beforehand) የወደ፡ ፊት፡ እቅድ

provisions ሥንቅ

provisional ጊዜያዊ

provoke (arouse) አስነሣ፤ ቀሰቀሰ ; (irritate) አስቆጣ

proximity ቅርበት፡ መሆን

prudence አስተዋይነት

prudent አርቆ፡ የሚያስብ

be prudent ተጠነቀቀ

pry ጠልቆ፡ ገባ

Psalms የዳዊት፡ መዝሙር

psychiatry የአእምሮ፡ ሕክምና

psychology የሥነ፡ ልቦና፡ ትምህርት

public (n.) ሕዝብ

in public በደባባይ

public (adj.) የሕዝብ

become public በይፋ፡ ታወቀ

make public በግልጽ፡ አስታወቀ

publication ጽሑፍ

publicly (openly) በደባባይ

(by the public) በሕዝብ፡ ዘንድ

public opinion የሕዝብ፡ አስተያየት

public school የመንግሥት፡ ትምህርት፡ ቤት

publish (a book) አሳተመ ; (make generally known) አዛመተ

publisher አሳታሚ

puddle የተቋጠረ፡ ውኃ፡

pugnacious ጠበኛ

pull ጐተተ ; (a tooth) ነቀለ

pull ahead ቀደመ

pull down (demolish) አፈረሰ ; (lower) አወረደ

pull out (vt.) ነቀለ

pull out, vi. (train) ተነሣ ; (troops) ለቆ፡ ወጣ

pull up (rocks) ነፍ፡ አደረገ

(a chair) ጠጋ፡ አደረገ

pulmonary የሳምባ

pulp ሥጋ

pulpit መስበኪያ፡ ሰገነት

pulsate ትር፡ ትር፡ አለ

pulse (n.) የልብ፡ ትርታ

pulverize (grind to a powder)
አደቀቀ ; (annihilate) አወደመ

pump (n.) ፓምፕ፡

pumpkin ዱባ

punch, v. (a ticket) በሳ ;
(in the nose) በቡጢ፡ መታ

punctual ሰዓት፡ አክባሪ

punctuate (use periods, commas)
ነጥብ፡ አደረገ ; ~~(interrupt)~~
~~አቋረጠ~~ (emphasize) አገነነ

punctuation ሥርዓተ፡ ነጥብ

puncture, v. (of a nail) በሳ ;
(of a needle) ወጋ

puncture (n.) ቡሳ

punish ቀጣ

punishment ቅጣት

pupil (student) ተማሪ ; (of eye)
የዓይን፡ ብሌን፤ የዓይን፡ ብሌት

puppet አሻንጉሊት

puppy ቡችላ

purchase (v.) ገዛ

purchase (the purchasing) መግዛት;
(something bought) የገዛው፡ ዕቃ

pure ንጹሕ ; (nonsense) ፈጽሞ; ;
(Amharic) የጠራ ; (heart) ቅን

purely (entirely) በሙሉ ;
(merely) ያህል

purgative የሚያስቀምጥ፡ መድኃኒት

purge (empty the bowels) አስቀመጠ ;
(rid of) አስወገደ

purge የሚያስቀምጥ፡ መድኃኒት

purify አጠራ

purity (being pure) ንጹሕ፡ መሆን;
(innocence) ንጽሕና

purpose ጉዳይ ; (need) ፍላጎት;
(aim) ያሰበው
on purpose ሆነ፡ ብሎ፤ ዐውቆ

purposely ሆነ፡ ተብሎ

purr አንጓረረ

purse ቦርሳ

pursue (follow) ተከታተለ ;
(chase) አሳደደ ; (harass)
አስቸገረ

pursuit መከታተል

pus መግል

push ገፋ ; (the button) ተጫነ;
(roots) ሰደደ ; (urge) ገፋፋ
push on ገሰገሰ

put (set in a certain place)
አስቀመጠ ; (insert) አስገባ;
(submit) አቀረበ ; (explain)
አስረዳ
put across አስረዳ
put aside አስቀመጠ
put back መለሰ

put down አወረደ ; (a name) ጻፈ ; (suppress) ደመሰሰ

put off አስተላለፈ

put on (weight) ክብደት፡ ጨመረ; (a dress) ለበሰ ; (glasses, hat, shoes) አደረገ ; (trousers) ←አጠለቀ

put out (publish) አወጣ ; (expel) አስወጣ ; (stretch out) ←ዘረጋ ; (extinguish) አጠፋ

put together አገጣጠመ

put up (hands) አነሣ ; (a notice) ለጠፈ

putrid, be --- ገማ

puzzle (v.) አደናገረ

be puzzled ግራ፡ ገባ(ው)

puzzle (n.) እንቆቅልሽ

python ዘንዶ

Q

quack (v.) አስካካ

quake (v.) ተንቀጠቀጠ

qualification(s) ብቁነት፤ ችሎታ

qualified (having the skills) ብቁ ; (limited, with some reservations) ገደብ፡ ያለው

qualify (make fit) አበቃ ; (give legal authorization) ፈቀደ(ለት); (limit in meaning) ገደብ፡ አበጀ(ለት)

quality (kind) ዓይነት ; (excellence) ጥሩነት፤ ተመራጭነት ; (attribute) ችሎታ

quantity መጠን ; (as against quality) ብዛት

quantities of ብዙ

what quantity? ምን፡ ያህል

quarrel (v.) ተጣላ

quarrel (n.) ጥል፤ ጠብ

quarrelsome ጠብኛ

quarter, n. (one fourth) ሩብ ; (a quarter of a dollar) ስሙኒ; (district) ሰፈር ; (mercy) ርኅራኄ

quarters (of soldiers) ሰፈር ; (lodging) ማረፊያ

quarter after three ዘጠኝ፡ ተሩብ

quarter to three ለዘጠኝ፡ ሩብ፡ ጉዳይ

quaver ተርገበገበ

queen ንግሥት

queenly የንግሥት

queer የሚገርም፤ እንግዳ

feel queer ተጨጨነ(ው)

quench (thirst) አረካ ; (fire) አጠፋ

querulous ነዝናዛ

query, v. (ask) ጠየቀ ; (feel doubt about) ትክክለኛ፡ መሆኑን፡ ተጠራጠረ

query (n.) ጥያቄ

quest ፍለጋ

question, vi. (ask) ጠየቀ ; (interrogate) መረመረ ; (doubt) ተጠራጠረ

question (n.) ጥያቄ ; (matter to be discussed) ጉዳይ ; (doubt) ጥርጣሬ

beside the question ከአርእስቱ፡ ውጭ

be beyond question አያጠራጥርም

without question ያለ፡ ጥርጥር

questionable አጠራጣሪ፤ የሚያጠራጥር

question mark የጥያቄ፡ ምልክት

questionnaire መጠይቅ

queue ሰልፍ

quick የተፋጠነ ; (worker) ፈጣን ; (mind) ንቁ ; (temper) ቁጡ

quicken (vt.) አፋጠነ

quickly ቶሎ፤ ቶሎ፡ ብሎ፤ ባንዴ

quicksilver ባዜቃ

quiet (vt.) ዝም፡ አሰኘ

quiet down ዝም፡ አለ ; (wind) ጸጥ፡ አለ ; (excitement) በረደ

quiet (n.) ጸጥታ

quiet (adj.) ጸጥተኛ፤ ጸጥ፡ ያለ; (life) ግርግር፡ የሌለበት; (colors) ደብዛዛ፡ ያለ

be quiet ዝም፡ አለ ; (town) ጭር፡ አለ ; (sea) ጸጥ፡ አለ

quietly ዝም፡ ብሎ፤ በጸጥታ

quit, v. (leave) ለቀቀ፤ ወጣ; (stop, cease) አቆመ ; (give up) ተወ

quite ፍጹም፤ በፍጹም፤ ሙሉ፡ በሙሉ; (to a certain degree) በጣም

quiver ተንቀጠቀጠ

quiz አጭር፡ ፈተና

quorum ምልአተ፡ ጉባኤ

quotation ጥቅስ

quotation mark ትእምርተ፡ ጥቅስ

quote ጠቀሰ ; (state) አለ

R

rabbit ጥንቸል

race, vt. (try to outdo in speed) ← በሩጫ፡ ተወዳደረ ; (enter in a contest) ለእሽቅድምድም፡ አቀረበ

race, vi. (run, horse) ጋለበ ; (run, children) ሮጠ ; (car) ← ከነፈ ; (participate in a contest) ተሽቀዳደመ

race, n. (group of people) ዘር ; (contest) የፈረስ፡ እሽቅድምድም

race course የሩጫ፡ መወዳደሪያ፡ ሜዳ

racial የዘር

racket (disturbing noise) ሁካታ ; (dishonest way of making a living) ማጭበርበር ; (tennis) ← ራኬት

make a racket ተንጫጫ

radiant (giving out rays) ብርሃን፡ የሚሰጥ;

(color) ደማቅ; (smile) ብሩህ

radiator (for heat) የቤት፡ ማሞቂያ; (of car) የሞተር፡ ማቀዝቀዣ

radical, adj. (fundamental) መሠረታዊ ; (extreme, in politics) [illegible]፡ ራካሪ፡ ተራማጅ

radio ሬዲዮ ፤ ራዲዮ

radio station ሬዲዮ፡ ጣቢያ

raft ማንሳፈፊያ፡ ታንኳ

rag ጨርቅ

rags ቡትቶ

rage, v. (express violent anger) በጣም፡ ተናደደ ፤ ጦፈ;

(of storm) ገሰ(በተ)

rage, n. (violent anger) ንዴት ;

(violence) ኃይለኛነት ;

(passing fashion) ተወዳጅ

ragged ቡትቶ፡ የለበሰ

ragged clothes ቡትቶ

raid (v.) ወረረ

raid (n.) ወረራ

rail, n. (railroad) ሐዲድ;

(horizontal bar) መደገፊያ

railing መደገፊያ

railroad ባቡር

railroad station ባቡር፡ ጣቢያ

railroad tracks የባቡር፡ ሐዲድ

reilway የባቡር፡ ሐዲድ፡

rain (v.) ዝናብ፡ ጣለ ፤ ዘነበ

rain (n.) ዝናብ

rains ክረምት

rainbow ቀስተ፡ ደመና

raincoat የዝናብ፡ ልብስ

rainy ዝናብ፡ የሚበዛበት

rainy season ክረምት

raise, v. (a monument) አቆመ ; (children) ወልዶ፡ አሳደገ; (breed) አረባ ; (wheat) አመረተ ; (bring to life) አስነሣ ; (promote) ከፍ፡ አደረገ ; (hand, question) አነሣ ; (the head) ← አቀና ; (increase) ጨመረ; (money, army) ሰበሰበ

be raised (promoted) አደገ ;

(increase) ጨመረ

raise, n. (in salary) የደምወዝ፡ ጭማሪ;

(promotion) እድገት

raisin ዘቢብ

rake, v. (ashes) ጫረ ; (leaves) [illegible]

ሰበሰበ ; (search carefully) በረበረ

rake (n.) ቅጠል፡ መጥረጊያ

rally (vi.) ተሰባሰበ ; (regain strength) አገገመ

ram (male sheep) በግ ; (pole) መስበሪያ

ramble (stroll without purpose) ወዲያ፡ ወዲህ፡ አለ ; (talk without consequence) ዘበረቀ

ramify ተከፈለ

rampage (v.) ፈረወጠ

rampage (n.), go on a ---
(children) ምስቅልቅሉን፡ አወጣ;
(army) በዘበዘ፤ ሕዝቡን፡ ፈጀ

ranch (of cattle) ከብት፡ ማርቢያ፡ መሬት;
(of fruit) እርሻ

rancid የሸገ

rancor ክፉ፡ ያለ፡ ምኞት

random, at --- እንደገኘ

range (vt.) ደረደረ

range, vi. (roam) ተዘዋወረ ; (be found) ተገኘ ; (vary within certain limits) ደረሰ

range (n.) መጠን ; (for cooking) ምድጃ

cattle range ከብት፡ ማሰማሪያ

rank (arrange in a row) መደበ ; (classify) ቆጠረ

rank above በማዕረግ፡ በለጠ

rank (n.) ማዕረግ

ransom (n.) ቤዛ፤ ማስለቀቂያ፡ ገንዘ

ransom (v.) ማስለቀቂያ፡ ቤዛ፡ ከፈለ

rap ደበደበ

rapacious (living on prey) አድኖ፡ የሚኖር ; (greedy) ቋንጃፋ

rapid ፈጣን

rapidly ቶሎ፡ ቶሎ፤ በፍጥነት

rare ብርቅ ; (unusual) ልዩ; (strange) እንግዳ ; (lightly cooked) በደንብ፡ ያልበሰለ

rarely አልፎ፡ አልፎ

rascal ወስላታ

rash, adj. (hasty) ችኩል ; (taking too much risk) አደገኛ

rasp (n.) ሞረድ

rasping ጎርናና

rat አይጥ

rate, v. (put in a certain class) ደረጃ፡ ሰጠ ; (regard) ~~ገመተ~~ ገመተ

rate (n.) ዋጋ

at any rate ያም፡ ሆነ፡ ይህ

rather እንዲያውም (rather, we will stay እንዲያውም፡ እንቆያለን)

ratify አጸደቀ

rating የደረጃ፡ ድልድል

ration (v.) እየመጠኑ፡ አከፋፈለ፤ እየቆጠበ፡ አደለ

ration የተወሰነ፤ ራሽን

rations ቀለብ

rational (be able to think) አስተዋይ፤ አእምሮ፡ ያለው;

(based on reason) በምርምር፡ የተደረሰበት

rattle (vi.) ተንገጫገጨ

rattle (n.) መንቀጫቀጭ;

(child's toy) የሚቅጨለጨል መጫወቻ

ravage, v. (of locust) አወደመ;

(of fire) አጠፋ

rave (talk in a disconnected manner) ቀዠ ; (talk with great enthusiasm) አድንቆ፡ ተናገረ

raven ቁራ

ravine ገደል

ravished, be --- ተመሰጠ

ravishing የሚማርክ

raw (meat, potatoes) ጥሬ ;

(milk) ያልተፈላ ; (vegetables) ያልተቀቀለ;

(wound) የተላጠ

raw materials ጥሬ፡ እቃ

ray ጨረ፤ ጨረር;

(of hope) ጭላንጭል

raze ድምጥማጡን፡ አጠፋ

razor ምላጭ

reach (v.) ደረሰ ; (hand) አቀበለ ;

(get to) አገኘ ; (the heart)

← ነካ

reach out እጁን፡ ዘረጋ

read አነበበ ; (the future) አየ ;

(man's heart) ዐወቀ

reader (who reads) አንባቢ ;

(schoolbook) የንባብ፡ መጽሐፍ

reading ንባብ

reading room የንባብ፡ ክፍል

ready (v.) አዘጋጀ

ready (adj.) ዝግጁ

be ready ተዘጋጀ ; (of dinner) ደረሰ

real እውነተኛ፤ ትክክል;

(genuine) ደንበኛ

real estate የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት

reality እውነት

realize (attain) ከፍጻሜ፡ አደረሰ;

(be aware) ተገነዘበ፤ ተረዳ;

(a profit) አገኘ

really በእውነቱ፤ በእርግጥ

realm ግዛት

realty የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት

reap አመረተ ; (a reward) አገኘ

reappear እንደገና፡ ብቅ፡ አለ

rear, vt. (bring up) አሳደገ ;
(breed) አረባ ; (raise up)
← ቀና፡ አደረገ

rear, n. ጀርባ ፤ ኋላ
in the rear ከ . . . በስተጀርባ

rear (adj.) የኋለኛ

reason (vt.) ገመተ ; (arrived at by means of logic) አመዛዝኖ፡ ደረሰበት

reason, vi. (urge logically) ← አስረዳ ; (think logically) ተመራመረ

reason, n. (motive) ምክንያት ; (ability to think) የማሰብ፡ ← ችሎታ ; (sanity) አእምሮ
bring (someone) to reason ← አግባባ

reasonable (person) አስተዋይ ; (price) መጠነኛ ; (choice) ← ተገቢ ; (offer) ደኅና

reasoning አስተሳሰብ

reassure (assure) አረጋገጠ ; (restore to confidence) አጽናና

rebate ቅናሽ

rebel (v.) በመቃወም፡ ዐመፀ

rebel (n.) ዐመፀኛ ፤ አጋዳሚ

rebellion ዐመፅ

rebellious (defying authority) ያመፀ ; (hard to manage)

← እንንከኝ፡ ባይ

rebound ነጥሮ፡ ተመለሰ

rebuild እንደገና፡ አሠራ

rebuke (v.) ገሠጸ

rebuke (n.) ነቀፌታ ፤ ግሣጼ

recalcitrant እምቢተኛ ;
(cattle) ለግመኛ

recall (remember) አስታወሰ ;
(take back) ነጠቀ

recant [illegible] ፤ ካደ

recapitulate እንደገና፡ ገለጸ

recede ወደ፡ ኋላ፡ ሸሸ

receipt (receiving) መድረስ ;
(written statement) ደረሰኝ
receipts ገቢ

receive ተቀበለ ; (welcome)
ተቀብሎ፡ አነጋገረ ;
(of radio) ሳበ ;

receiver (who received) ተቀባይ ;
(of telephone) የስልክ፡ መነጋገሪያ

recent የቅርብ ; (happening recently) በቅርቡ፡ የሆነ

recently በቅርብ ጊዜ

receptacle የሚከትበት፡ እቃ

reception (receiving) መቀበል ;
(greeting) አቀባበል ; (formal entertainment) ግብዣ

reception desk የእንግዶች፡ መቀበያ፡ ቦታ

receptionist አስተናጋጅ

recess ዕረፍት

recipe (for food) ያሠራር፡ መምሪያ። የምግብ፡ መምሪያ;
(plan for doing anything) ሐሳብ

reciprocal የጋራ

reciprocate (wishes) አጸፋ፡ መለሰ;
(with a gift) ውለታውን፡ መለሰ

recite (prayers) ደገመ። አደረሰ;
(poetry) አሰማ ; (a lesson) በቃሉ፡ ወጣ

reckless ግዴየለሽ

reckon (count) አሰበ ; (consider, judge) አድርጎ፡ ቈጠረ ;
(count on) ተማመነ ; (think) ← መሰለ(ው)

reckoning ግምት
day of reckoning የመጨረሻይቱ፡ ቀን፡

recline ጋደም፡ አለ

recognition መታወቅ
find recognition ስሙ፡ ተጠራ

recognize ለየ። ዐወቀ

recollect አስታወሰ

recollection ትዝታ። የሚያስታውሰው፡ ነገር

recommend (counsel) አዘዘ ; (write favorably of) በጎ፡ መሆኑን፡ መሰከረለት
(suggest) አሳሰበ። ሐሳብ፡ አቀረበ
recommend to one's care አደራ፡ ሰጠ፡

recommendation (advice) የሚመክር;
(written praise) አስተያየት

recompense, v. (reward) ውለታውን፡ ← ከፈለ ; (make amends for) ተካ

recompense, v. (reward) ውለታውን፡ ከፈለ ; (make amends for) ተካ

recompense (n.) ካሳ

(be reconciled ታረቀ

reconcile አስታረቀ ; (bring into agreement) አስማማ

reconciliation እርቅ

reconsider እንደገና፡ ተመለከተ

reconstruct እንደገና፡ ሠራ

record, v. (keep for remembrance) አሰፈረ ; (set down in writing) ጻፈ ; (register) ሰካ ; (on tape) ቀዳ

record, n. (official document) መዝገብ ; (of student) ሪፖርድ ; (for phonograph) ሸክላ ; (in sport) ክብረ፡ ወሰን
keep a record of መዘገበ

recording የተቀዳ፡ ሙዚቃ

record player የሸክላ፡ መጫወቻ

recover, vt. (get back again) ~~አስመለሰ~~

አስመለሰ ; (damages) ካሳ፡ አገኘ

recover (vi.) ዳነ

recovery (of a lost thing) ማግኘት ; (of health) ማገገም፤ መዳን

recruit, v. (enlist) መለመለ ; (get new members) አሰገበ

recruit (n.) ምልምል፡ ወታደር

rectify አስተካከለ

recuperate አገገመ

recur ተቀሰቀሰ(በሽ)

red ቀይ

be in the red እዋበሰለ፡ ዕዳ

Red Cross ቀይ፡ መስቀል

redeem (regain possession) አስመለሰ ; (fulfill) ፈጸመ ; (free) ገንዘብ፡ ከፍሎ፡ ነጻ፡ አወጣ

red-hot, be --- ጋለ

redouble [illegible]ጥፍ፡ አደረገ

redress አረመ

reduce, vt. (decrease) ቀነሰ ; (degrade) ዝቅ፡ አደረገ ; (conquer) ድል፡ አድርጎ፡ ያዘ ; (bring to a situation) አደረሰ

reduce, vi. (in weight) ክብደት፡ ቀነሰ

reduplicate አበዛ

reed መቃ

reel, v. (seem to rock) ዞረ ; (stagger) ተግታረታረ

reel (n.) ምቅል

refer (submit) አቀረበ ; (direct for information) እንዲመለከት፡ መራ

refer to (turn for information) ተመለከተ ; (cite) ጠቀሰ ; (make allusion) ነካ፡ አነሣ

reference (statement to which attention is directed) መግለጫ ; (statement about someone's ability) የምስክር፡ ወረቀት ; (person who can give information about someone's character) ተጠያቂ

make reference to አነሣ

refill (a jar) አጠጣ ; (a tank) በንዚን፡ ሞላ

refined የጠራ

reflect, vt. (show like a mirror) ገለጸ ; (of mirror) አሳየ ; (of glass) አንጸባረቀ

reflect (vi.) አሰበ

reflex action ሳይታሰብ፡ የሚደሆን፡ ድርጊት

reform (v.) አሻሻለ

reform (n.) መሻሻል፤ ለውጥ

refractory (child)) ግትር;

(ox) ለግመኛ

refrain (v.) ተቆጠበ

refresh (of bath) አነቃቃ ;

(of rain) አረጠበ

refrigerator ማቀዝቀዣ

refuge (place of safety) ጎሬ ;

(safety) ደኅንነት

take refuge ተደብቆ፡ ቆየ

refugee ስደተኛ፤ ጥገኛ

refusal እምቢታ፤ እምቢ፡ ማለት

give a refusal እምቢ፡ አለ

refuse (v.) እምቢ፡ አለ; ~~nega~~ or expressed by negative verb (he ~~tive verb~~ refused to sign አልፈረመም)

refuse (n.) ቆሻሻ

regain (recover) አስመለሰ ;

(reach again) አገኘ

regal ንጉሣዊ

regale አስደሰተ

regalia የክብር፡ ልብስ

regard, v. (consider) ቆጠረ ;

(concern) ተመለከተ ;

(respect) ጠበቀ ; (admire)

← አከበረ ; (accept) ተቀበለ

regard (n.) ዓይን

regards) ሰላምታ

in regard to ስለ

in that regard በዚህ፡ ረገድ

regardful, be --- ተጠነቀቀ

regarding ስለ፡

regency እንደራሴነት

regent እንደራሴ

regime (system of government)

መንግሥት ; (period of rule)

ዘመን

regiment ሬጂመንት

region ቀበሌ፤ ክፍለ፡ ሀገር

regional, የቀበሌ

register (vt.) መዘገበ

register, (vi.) ተመዘገበ ;

(show) ታየ

register (n.) መዝገብ

registered letter ሪኮማንዴ

registration (registering)

መመዝገቢያ ; (of automobile) የባለቤትነት፡ መታወቂያ

regress ዝቅ፡ አለ

regret (v.) ተጸጸተ

regret (n.) ጸጸት

regrets የቅርታ፡ መጠየቅ

regrettable የሚያሳዝን

regular (n.) ደንበኛ

regular, adj. (price) ደንበኛ

(habits) የተወሰነ ; (place)

የተለመደ ; (work) ቀዋሚ፤ ቋሚ

(features) የተስተካከለ

regularly ሳይቋርጥ፤ ያለማቋረጥ

regulate ወሰነ፤ ተቈጣጠረ

regulation (rule) ደንብ ; (control) መቈጣጠር

rehearse ተለማመደ

reign, v. (rule) ነገሠ ; (prevail) ሰፈነ፡

reign (n.) አገዛዝ ; (period of rule) ዘመነ፡ መንግሥት

reimburse ተካ(ከፈ)

rein (of horse) ልጓም ; (means of control) ሥልጣን

reinforce አጠናከረ

reinforcements ተጨማሪ፡ ጦር

reiterate ደገመ

reject (refuse to take) አልተቀበለም ; (discard) ጣለ

rejoice (vt.) አስደሰተ

rejoice (vi.) ተደሰተ

relapse, v. (backslide) ተመለሰ; (fall back into illness) አገረሸ

relate (tell) አወራ ; (associate) አዛመደ

related (adj.) የተዛመደ

be related ተዛመደ ; (connected in some way) ተያያዘ

relation (narrating) የነገረው፡ ነገር (relatives) ዘመድ፡ (connection) ግንኙነት

relationship ግንኙነት

family relationship ዝምድና

relative (n.) ዘመድ

relative (adj.) የተያያዘ

relatively በመጠኑ

relax, vt. (efforts) ቀነሰ ; (ease) መንፈስን፡ አረካ; (requirements) አላላ

relax (vi.) ዕረፍት፡ አገኘ፤ ተዝናና

relay አስተላለፈ

release, v. (set free) ለቀቀ ; (from vows) ፈታ ; (from a promise) ማረ ; ~~(surrender)~~ (give up the title to) — አዛወረ ; (a bomb) እንዲፈነዳ ለቀቀ

relegate, (turn over) አስተጓጓለ (remove) አስቀመጠ

relent ለሰ፡ አለ

reliable (source) የታመነ ; (servant) ታማኝ ; (firm) እምነት፡ የሚጣልበት

relic ቅርስ

relief (aid) እርዳታ ; (freeing from a pain) ፋታ ; (person who relieves another from duty) ተቀያሪ ; (rest) ዕረፍት

feel relief [illegible]፡ እፎይ፡ አለ

relieve (a headache) አሻለ፤ አስታገሠ
(aid) ረዳ ; (the fort) ~~[illegible]~~ ተከላከለ ; (alleviate) ~~[illegible]~~ አቃለለ ; (release from a post) ቀየረ

religion ሃይማኖት

religious (person) ሃይማኖተኛ;
(differences, order) የሃይማኖት

religious service የጸሎት፡ ሥነ፡ ሥርዓት

relinquish ለቀቀ፤ ተወ;
(hope) ቈረጠ

reluctant, be --- ፈቃደኛ፡ አልነበረም

rely አመነ፤ ተማመነ፤ እምነት፡ ጣለበት

remain (be left) ቀረ ; (stay) ~~[illegible]~~ ቆየ

remainder የቀረ፤ ቀሪ

remaining የተረፈ

remains (of meal) የተረፈ ; (of a dwelling) ፍርሽ ; (dead body) አስከሬን

remark, v. (notice) አየ፤ ተረዳ;
(say briefly) ተናገረ

remark (n.) አስተያየት

remarkable የሚያስደንቅ፡ ነገር፤ የሚደነቅ

remedy (v.) አሻሻለ

remedy, n. (cure) መድኃኒት;
(solution) መፍትሔ

remember, vt. (recall) አስታወሰ;
(not forget) አልረሳም፤ አልዘነጋም
remember (vi.) የማስታወስ፡ ችሎታ፡ አለው

remembrance (gift or token) ማስታወሻ ; (remembering) ትዝታ

remind አስታወሰ

reminder ማስታወሻ

reminiscence ትዝታ

remission ምሕረት

remit (send) ላከ ; (pay) ከፈለ ;
(sins) ነጻ፡ አደረገ;
(efforts) ቈጠበ
remit (vi.) ተቀነሰ
be remitted (of a matter) ~~[illegible]~~ ተላለፈ ; (taxes) የ··· ምሕረት፡ ተደረገ

remnants ትራፊ፤ የቀረ

remorse ጸጸት

remote ሩቅ
be remote ራቀ

removal (removing) ማንሳት ;
(being removed) መነሳት

remove (ink stains) አስለቀቀ ;
(a bullet) አወጣ ;

(from office) አስወጣ ; (a tooth) ነቀለ ; (hat) አወለቀ;
(doubt) አስወገደ

remunerate ዋጋ፡ ከፈለ

remuneration ዋጋ

rend ቀደደ

render (make) አደረገ ; (submit) አቀረበ ; (translate) ተረጐመ;
(a part in a play) ሠራ

renegade ከዳተኛ

renew (a lease) አሳደሰ;
(a passport) አደሰ ; (an attack) እንደገና፡ ጀመረ;
(friendship) ቀጠለ

renounce (disown) ካደ ;
(give up) በፈቃዱ፡ ተወ

renovate አሳደሰ

renown ዝና

renowned የታወቀ

rent, vt. (hire) አከራየ ;
(lease) ተከራየ

rent, n. (of room) ኪራይ ;
(torn place) ቀዳዳ
be for rent ተከራየ

rental ኪራይ

reorganize እንደገና፡ መደበ፤ እንደገና፡ አደራጀ

repair (v.) ጠገነ ; (make up for) ካሰ፤ አሟላ

repair (n.) ጥገና

reparations የጦር፡ ካሳ

repay ከፈለ ; (a favor) መለሰ

repeal ሻረ

repeat (say again) ደገመ ; (say what someone else has said) ← አወራ ; (a secret) አወጣ

repeatedly ደጋግሞ

repel (drive back) መለሰ ;
(disgust) አስከፋ ; (refuse to accept) አልቀበልም፡ አለ
(water) አላስገባም

repent ተጸጸተ

repentance ጸጸት

replace (put back) መልሶ፡ አስቀመጠ;
(fill the place of) በሱ፡ ቦታ፡ ተካ

reply (v.) መለሰ

reply (n.) መልስ

report, v. (relate) አተተ ;
(make a report) ገለጸ፤ መግለጫ፡ ← ሰጠ ; (announce) አስታወቀ;
(denounce) አሳበቀ፤ ነገረ(በት)

report (n.) መግለጫ;
(rumor) ወሬ

report card የተማሪ፡ ማመልከቻ

reporter ጋዜጠኛ፤ (~~ወሬ~~)፡ ዜና አቀባይ

repose, vi. (lie at rest) ጋደም፡ አለ ; (rest on a support) ተተካ

repose, n. (peace and quiet)
ሰላምና፡ ጸጥታ
(rest) ዕረፍት ·

reprehend ወቀሰ

represent (describe) ገለጸ ;
(portray) አሳየ ; (act for)
ወከለ ; (act the part of)
ተመስሎ፡ ሠራ; (stand for)
አመለከተ ; (be an example
of) ምሳሌ· ነው

representation መግለጫ

representative, n. (delegate)
መልእክተኛ;
(agent) ወኪል

repress (mutiny) ደመሰሰ ;
(laughter) ገታ ; (talent) ቀጣ

reprimand ገሠጸ

reprint እንደገና፡ አተመ

reprisal በደል

reproach (v.) ወቀሰ

reproach, n. (blame) ወቀሳ ;
(cause for blame) አሳፋሪ

reproduce, vt. (reproduce again)
ቀዳ ; (shown) አሳየ
reproduce, vi. (produce offspring) ተራባ

reprove ገሠጸ

republic ሪፐብሊክ

repudiate (a statement) ካደ ;
(one's wife) ፈታ

repugnant (odor) መጥፎ ;
(offensive) አስከፊ

repulse (repel) መከተ ;
(reject) ናቀ

repulsion, feel --- for ቀፈፈ(ው)

repulsive ቀፋፊ

reputable ስመ፡ ጥሩ

reputation ዝና ፣ ስም

repute ዝና

request (v.) ጠየቀ

request (n.) ልመና ፣ የተጠየቀ
make a request for ጠየቀ

require ጠየቀ ፣ ፈጀ
(order) አዘዘ ; (need) አስፈለገው
(

requirement (necessity) አስፈላጊ·
ነገር ; (something required)
የተደነገገ፡ ደንብ

requisition (n.) መጠየቂያ

rescind ሻረ

rescue (v.) አዳነ ፣ አተረፈ

research (v.) መረመረ

research (n.) ምርመራ ፣ ጥናት

resemblance መመሳሰል

resemble መሰለ

resent ቅር፡ አለው ፣ ተቀየመ

resentful, be --- ቅር ፡ አሰኘ

resentment ቅሬታ

reservation (securing of a place) ቦታ ፡ መያዝ ; (secured place) የያዘው ፡ ቦታ ; (a limiting condition) ገደብ

reserve, v. (secure a place) ያዘ; (save) ቈጠበ ፤ አስቀመጠ; (set apart) መደበ ; (postpone (a decision)) ለሌላ ጊዜ ፡ አስተላለፈ

reserve, n. (something stored) ተቀማጭ ፤ መጠባበቂያ; (tract of land set aside for special use) ክልል ; (restraint) ገለልተኛነት

without reserve በሙሉ ፡ ልብ

reserved, adj. (restrained) ጭምት

reservoir ማጠራቀሚያ ፤ የውኃ ፡ ማጠራቀሚያ; (source) ምንጭ

reside ኖረ

residence (dwelling) መኖሪያ ; (fact of residing) መቀመጫ; (legal domicile) አድራሻ

resident, be --- ኖረ

residential የመኖሪያ

residue የተረፈ ; (of oil) ዝቃጭ

resign ሥራውን ፡ በፈቃዱ ፡ ለቀቀ; (from a club) ወጣ

resign oneself ግድ ፡ ሆነብኝ

resignation (act of resigning) ከሥራ ከመሰናበት ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ; (written statement) የሥራ ፡ መልቀቂያ ፡ ደብዳቤ; (quiet submission) ትዕግሥት

resin ሙጫ

resist ተቋቋመ ; (try not to yield to) ገታ

resistance ተቃውሞ ፤ መከላከል; (power of resistance) የመቋቋም ፡ ኃይል

offer resistance ተቋቋመ

resolute ቈራጥ

resolution (determination) ~~[illegible]~~ ቍርጠኝነት ; (thing decided on) ቍርጥ ፡ ሐሳብ ; (formal expression of opinion) ውሳኔ ; (solution) መፍትሔ

resolve, v. (decide) ቈረጠ ; (decide by vote) ወሰነ ፤ ውሳኔ ፡ አስተላለፈ; (solve) መፍትሔ ፡ አስገኘ; (break up) ከፈለ ፤ አለያየ

resolve (n.) ቈራጥነት ፤ ቍርጠኝነት

resort, n. (place people go to) ← የመዝናኛ ፡ ቦታ

(recourse) ረዳት

resound አስተጋባ

resource (resort) መጠጊያ ፤ የመጨረሻ፡ ማምለጫ፡ ዘዴ;

(resort in money) የገቢ፡ ምንጭ

resources ሀብት ፤ ሀብቶች

natural resources የተፈጥሮ፡ ሀብት

resourceful ዘዴኛ

respect, v. (honor) አከበረ ; (admire) አደነቀ ; (show consideration) ጠበቀ ; (concern) ተመለከተ

respect, n. ክብር ; (respecting) አክብሮት

respects ሰላምታ ፤ አክብሮት

in every respect በማንኛውም፡ ረገድ

in many respects በብዙ፡ መንገድ

show respect አከበረ

respectable (deserving respect) የተከበረ ; (having a good reputation) መልካም ; (clothes) ተስማሚ ; (amount of money) ከፍ፡ ያለ ; (score) ደኅና

respectful ትሕትና፡ የተሞላበት

be respectful toward አከበረ

respectfully በአክብሮት

respective እየ + noun

respectively እንደ፡ ቅደም፡ ተከተላቸው

respiration ትንፋሽ

respite ፋታ

resplendent, be --- (uniform) ← አንጸባረቀ ; (person) ← አሸበረቀ

respond መለሰ

response መልስ

responsibility ኃላፊነት

responsible ኃላፊ ; (involving responsibility) ታላቅ፡ ኃላፊነት፡ ← ያለበት ; (accountable) ~~[illegible]~~ ← ተጠያቂ ; (reliable) ታማኝ

be responsible በኃላፊነት፡ ተጠየቀ;

(be the cause) ምክንያት፡ ሆነ

rest, vt. (give relief) አሳረፈ ; (lean) አስደገፈ; (base) መሠረተ

rest, vi. (take a rest, relax) ← ዐረፈ ፤ እፎይ፡ አለ; (lie down) ጋደም፡ አለ ; (lean) ← ተደገፈ; (be based) ተመሠረተ ፤ ← በ . . . ላይ፡ ነው; (be buried) በሰላም፡ አረፈ

rest, n. (ease, lack of motion) ← ዕረፍት ; (residue) የቀረ

be laid to rest ተቀበረ

come to rest ዐረፈ ; (stop moving) ቆመ

take a rest ዕረፍት፡ አደረገ

restaurant ምግብ፡ ቤት

restful, be --- ዕረፍት ሰጠ

restitution (act of giving back) ←መመለስ ; (act of making good any loss) ካሣ፣ ምትክ

restless, get --- ተቅነጠነጠ

restoration (of building) እድሳት ; (of independence) ←መመለስ

restore (put back to a former position) መለሰ ; (give back) ←መልሶ፡ ሰጠ ; (reestablish) ←እንደገና፡ አደረገ

be restored (of a building) ታደሰ

restrain (anger) ገታ ; (a dog) ያዘ

restrict ወሰነ

restriction ገደብ፣ ቁጥጥር

restroom ሽንት፡ ቤት

result, v. (happen from a cause) መጣ ; (become a cause) ምክንያት፡ ሆነ

result in አስከተለ

result (n.) ውጤት

resume, vt. (a journey) ቀጠለ ; (reading) ጀምሮ፡ ቀጠለ; (the seats) እንደገና፡ ያዘ

resurrect (the dead) እዳነ ; (a plan) እንደገና፡ ሠራበት

be resurrected ተነሣ

resuscitate ትንፋሽ፡ መለሰ

retail (vt.) ቸረቸረ

retail (n.) ችርቻሮ

retail dealer ቸርቻሪ

retain (hold) ያዘ ; (remember) አስታወሰ ; (a lawyer) ገዛ

retaliate አጸፋውን፡ መለሰ

retaliation አጸፋ

retard (keep back) ወደ፡ ኋላ፡ ጎተተ; (delay) አዘገየ

retell መልሶ፡ አወራ

reticent, ዝምተኛ

retinue የክብር፡ ተከታዮች

retire, vt. (remove from office after a long service) ጡረታ፡ አስገባ ; (withdraw) አስወገደ

retire, vi. (give up an office) ጡረታ፡ ገባ ; (stop working) ሥራውን፡ አቆመ ; (retreat) ተመለሰ ; (go to bed) ተኛ ; (to the library, convent) ገባ

retire for the night ተኛ

retired, adj. (civil servant) ጡረታ፡ የወጣ ; (doctor) ሥራውን፡ ያቆመ

retirement ጡረታ

retiring ዓይነ፡ አፋር፣ ዝምተኛ

retrace (trace back to an origin) ቈጠረ ; (trace over again) እንደገና ሣለ

retract (a statement) አጠፈ ; (the wheels) ሰበሰበ

retreat, v. (fall back) ወደ፡ ኋላ· አፈገፈገ ; (go for privacy) ለዕረፍት· ሄደ

retreat, n. (withdrawal) ማፈግፈግ ; (place for refuge) የማምለጫ፡ ቦታ

beat a retreat አፈገፈገ

retrieve (regain) አገኘ ; (make good) አረመ ; (of dog, find and bring back) ፈልጎ፡ አመጣ

retrogress ተመለሰ

return, vt. (give back, answer) መለሰ

return, vi. ተመለሰ

return, n. (coming back) መመለስ፤ (profit) ትርፍ

returns ውጤት

return ticket የመመለሻ· ቲኬት

in return ለዋጋ

reunify መልሶ፡ አዋሐደ

reunion አንድ፡ ላይ፡ መገናኘት

reunite አንድ፡ አደረገ፤ አገናኘ

be reunited (former enemies) እንደገና፡ ተዋሐዱ ; (mother and child) እንደገና፡ ተገናኙ

reveal (disclose) ገለጸ ; (a secret) አወጣ ; (show) ←አሳየ

revel ፈነጠዘ

revelation (revealing of a secret) ማውጣት ; (God's disclosure of Himself) ራእይ

revelry ፈንጠዝያ

revenge (v.) ተበቀለ

revenge (n.) በቀል

take revenge on ተበቀለ

revenue ገቢ

revere በጣም፡ አከበረ

reverence (n.) ማክበር

hold in reverence አከበረ

reverend አባ

reverent ሰው፡ አክባሪ

reverse, n. (opposite) ተቃራኒ ; (of coin) ጀርባ ; (defeat) ←ጉዳት ; (financial) ኪሳራ

revert ተመለሰ

review, v. (troops) ጎበኘ ; (a decision, events) መረመረ ; (a lesson) ከለሰ ; (a book) ←ትችት፡ ጻፈ

review, n. (of army) ሰልፍ ; (of a book) ትችት ; (of events) ምርመራ ; (of a lesson) ክለሳ

review lesson ከለሰ

revile ሙልጭ፡ እያረገ፡ ሰደበ

revise (change) ለወጠ ;
(improve) አሻሻለ

revision ማሻሻል

revival ማንሰራራት

revive, vt. (refresh) አነቃቃ;
(bring back to life) ነፍስ፡ ዘራበት ; (a custom) ሕይወት፡ ሰጠ ; (memories) አስታወሰ

revive, vi. (of spirit) ተነቃቃ ;
(of hope) ታደሰ ; (of flower) እንደገና፡ ለመለመ

revoke (a license) ነጠቀ ; (a concession) ሰረዘ

be revoked (annulled) ተሻረ ;
(repealed) ተነሣ

revolt (vt.) ዘገነነ

→revolt, vi. (rise up against authority) ዐመፀ ; (rebel) ←አሻፈረኝ፡ አለ ; (not accept) አልተቀበለም

revolution ሽብር፤ መሠረታዊ፡ ለውጥ
(any far-reaching change) ከፍተኛ፡ ለውጥ;
(revolving) መሽከርከር

revolutionary (n.) ደመ፡ ነውጠኛ

revolutionary, adj. (leader) ዓመፀኛ ; (causing a great change) ከፍተኛ፡ ለውጥ፡ የመጣ

revolutionize ከፍተኛ፡ ለውጥ፡ አስጠ

revolve (move in a circle) ዞረ,
(occur regularly) ተፈራረቀ

revolver ሽጉጥ

revulsion ጥላቻ

reward, v. (loyalty) ወሮታ፡ ከፈለ;
(workers) ዋጋውን፡ ከፈለው

reward (n.) ሽልማት፤ ዋጋ

rheumatism ቁርጥማት

rhinoceros አውራሪስ

rhyme (n.) ቤት፡ መምቻ

without rhyme or reason
ያለ፡ ምክንያት፤ በመሰለት፡ ተነሣሽ

rhythm ውዝዋዜ

rib ጎድን ; (of umbrella) ሽቦ

ribbon (for hair) ሪበን ;
(for dress) ጥብጣብ ; (for typewriter) ሽር

rice ሩዝ

rich (person) ሀብታም፤ ባለጸጋ;
(soil) ለም ; (fabrics) ውድ ;
(voice) ጥሩ ; (color) ደማቅ

get rich ከበረ

riches ሀብት

rid አጠፋ

get rid of (a person) ተገላገለ ;
(bad habits) ተላቀቀ

riddle እንቆቅልሽ

ride, vt. (a motorcycle) ነዳ ;
(a horse) ጋለበ ; (a mule)
← ተቀመጠ

ride (n.) ጉዞ

ridge (long mountain) ተረተር ;
(in the ground) ጉልም

ridiculous (person) ሞኛ ;
(hat) የሚያስቅ ; (price)
← የማይታመን

rifle ጠበንጃ ፣ ጠመንጃ

rift ስንጥቅ

right, n. (privilege) መብት ;
(correct thing) ደግ ;
(opposite of left) ቀኝ;
(conservative in politics)
ቀኝ፡ ክፍል

right, adj. (proper) ተስማሚ፣ተገቢ;
(correct) ልክ ; (opposite
of left) የቀኝ፡ እጅ

right, adv. (opposite of left)
ወደ፡ ቀኝ ; (correctly) ልክ፣
ትክክል ፣ በትክክል;
(directly) በቀጥታ
right away አሁኑኑ
right now አሁን
all right ደኅና ፣ እሺ

righteous መልካም

rightful (heir) ሕጋዊ፣ እውነተኛ;
(property) በሕግ፡ የሚገባ

right-hand (adv.) ወደ፡ ቀኝ
in the right-hand በቀኝ፡ በኩል

rightly (suitably) በሚገባ;
(correctly) በትክክል

right-of-way የመንገድ፡ ቅድሚያ

rigid (rule) ጥብቅ፣ ደረቅ
(strict) ደረቅ

rigor (of war) መከራ ; (of
heat) ብርታት

rigorous (discipline) ጥብቅ;
(method) በጣም፡ ትክክል

rim (of a glass) አፍ ; (of
eyeglasses) ክፈፍ ; (of
tire) ቸርኬ

rind ልጣጭ

ring, vt. (the bell) ደወለ ;
(coins) አቃጨለጨለ
ring (vi.) ደወለ ; (of a
doorbell) ተደወለ ; (of
phone) ጮኸ ; (of ears)
ጭው፡ አለ

ring, n. (for finger) ቀለበት ;
(for key) ዘለበት ; (of

bell) ድምፅ ; (circle) ክበብ ; (of circus) ~~[illegible]~~ ሰፈር ; (of spies) ቡድን

ring finger የቀለበት፡ ጣት

rinse (a pot) አለቃለቀ; (the mouth) ተጉመጠመጠ

riot (v.) በጠበጠ

riot (n.) ሁከት ፤ ሽብር

rioting ጸጥታ፡ ማደፍረስ

riotous የተረበሸ ፤ ረባሽ

rip (cloth) ቀደደ ; (a seam) ተረተረ

ripe የበሰለ

be ripe በሰለ

ripen አበሰለ

rise (v.) ተነሣ ; (of sun) ወጣ; (of price) ጨመረ ; (of river) ሞላ ; (of dough) ኩፍ፡ አለ; (come into view) ታየ ; (achieve higher rank) አደገ

rise, n. (small hill) ጉብታ ; (of river) መሙላት ; (of prices) መጨመር

give rise to አስነሣ ፤ አስከተለ

risk, --- one's life በነፍሱ፡ ቈረጠ

rite ሥነ፡ ሥርዓት

ritual (n.) ሥነ፡ ሥርዓት ፤ የሃይማኖት፡ ሥነ፡ ሥርዓት

rival, v. (be a match for) ← ተወዳደረ ; (compete with) ተፎካከረ

rival (n.) ተወዳዳሪ

rivalry ተፎካካሪነት ፤ ፉክክር

river ወንዝ

river basin የወንዝ፡ ሸለቆ

road መንገድ

roam (of a person) ተንቀዋለለ; (of animals) ተዘዋወረ

roar (v.) ጮኸ ; (of a lion) አገሣ ; (with laughter) ከት፡ ብሎ፡ ሣቀ

roar (n.) ጩኸት ፤ ድምፅ; (of a lion) ግሣት

roast, v. (meat) ጠበሰ; (coffee) ቈላ

roast (n.) ጥብስ፡ ሥጋ

roasted grain ቆሎ

roasting pan መጥበሻ

rob ዘረፈ

robber ቀማኛ

robbery ቀማኛነት ፤ ዘረፋ ፤ ስርቆት

robe (v.) አለበሰ

robe (n.) ልብስ ; (garment that shows neck) ካባ

robust ጠንካራ

rock, vt. (move) አወዛወዘ;

(cause to shake) አናጋ፤ አነቃነቀ

rock, vi. (in a chair) [illegible] ተወዛወዘ; (of a boat) ዋለለ

rock (n.) ቋጥኝ፤ ድንጋይ፤ አለት

rocket መንኰራኩር

rocking chair የሚወዛወዝ፡ ወንበር፤ ተወዛዋዥ፡ ወንበር

rocky (cliff) ቋጥኝ፡ የበዛበት; (road) ድንጋያማ፤ ኰረኰንቻማ; (shaky) የሚነቃነቅ

rod ዘንግ

rogue ወስላታ

role ስፍራ፤ ቦታ

roll, vt. (wrap around) ጠቀለለ; (dough) አሞለሞለ ; (a marble, eyes) አንከባለለ ; (of waves rolling the ship) ← አንገላታ

roll, vi. (of thunder) አጉረመረመ [illegible] (be wrapped) ተጠቀለለ፡ (of tears) ኮለል፡ አለ; ← (of a ship) ዋለለ፤ እየተወዛወዘ፡ ዘለቀ;

(of a ball) ተንከባለለ

roll by ተሽከረከረ

roll up (a rug) ጠቀለለ ; (an umbrella) [illegible]ጠፈ

roll, n. (of thunder) ድምፅ ; (of wrapping paper) ጥቅል ; (of bread) ድቡልቡል፡ ዳቦ

rolls መዝገብ

call the roll ስም፡ ጠራ

roller skate መንሸራተቻ፡ ጫማ

roof ጣራ፤ ጣሪያ

roof of the mouth ላንቃ

room (v.) ኖረ

room (n.) ክፍል — ; (space) ቦታ

room and board ምግብና፡ መኝታ

ladies' room የሴቶች፡ ሽንት፡ ቤት

men's room የወንዶች፡ ሽንት፡ ቤት

roomy ሰፊ፡ ቤት

rooster አውራ፡ ዶሮ

root, vt. (implant, fr. fear) አሰቀረ

root, vi. (begin to grow) ሥር. ← ሰደደ ; (turn over and dig up soil) አነፈነፈ

root up ነቃቀለ፤ መነቃቀል

root, n. (of tree) ሥር ; (source) ምንጭ

take root ሥር፡ ሰደደ

rope (v.) በገመድ፡ ጠለፈ

rope (n.) ገመድ

rosary መቍጠሪያ

rose ጽጌ፡ ረዳ

roster መዝገብ

rot (vt.) አበሰበሰ

rot (vi.) በሰበሰ

rotate, vi. (move around) ዞረ ; (change in regular order) ← ተለዋወጠ

rotation (of office) ተራ

rote, by --- በቃል

rotten (decayed) የበሰበሰ ; (corrupt) የተበላሸ

be rotten በሰበሰ

rough (fur) ሻካራ ; (wood) ያልተላገ ; (road) ኮረኮንች ; (skin of fruit) ወፍራም ; (work) ከባድ ; (voice) ጎርናና ; (times) አስቸጋሪ ; (manner) ባለጌ፤ የብልግና ; (life) ምቾት፡ የጎደለ

rough life, rough times የችግር፡ ጊዜ

roughly (in a rough manner) በንዴት፡ ቃል ; (approximately) በግምት

round (v.) ክብ፡ አደረገ; (the lips) አሞጠሞጠ

round off አስተካከለ

round up ሰበሰበ

round, n. (in sport) ዙር

make the rounds (of watchman) ← እየተዘዋወረ፡ ጠበቀ; (of policeman) [illegible] ; (of a doctor) እየዞረ፡ በሽተኞችን፡ ← ጎበኘ

round, adj. (number) ሙሉ፡ ቁጥር፤ ← ሙሉ፡ የተጠጋጋ; (ball) ← ድቡልቡል; (table) ክብ

round (adv.) በሙሉ

go round ዞሮ፡ ሄደ ; (news) ናፈሰ

in round figures በግምት

roundabout ዘወርዋራ፤ የዞረ

round trip ደርሶ፡ መልስ

rouse (awaken) አነቃ ; (stir up) ስሜት፡ ቀሰቀሰ

rout ድል፡ አድርጎ፡ በታተነ

route (n.) መንገድ

routine ልማድ

rove ተዘዋወረ

row (v.) ቀዘፈ

row, n., rhymes with 'low' (line) ← ተርታ ; (of horses) መደዳ ; (of seats) ረድፍ

row, rhymes with 'how' (loud voice) ጫጫታ ; (noisy argument) አምባጓሮ

royal ንጉሣዊ ; (welcome) ንጉሥ፡ ያክ

His Royal Highness ልዑል

royalty (kings and their ~~ንጉሣውያን~~ families) ንጉሣውያን፡ ቤተ፡ ሰብ ; (position of king) ንጉሠነት ; (payment made to an author) ← የደራሲ፡ ዋጋ

rub, vt. (back) እሽ ; (hands) ← እሽሽ ; (polish) ወለወለ; (cause to be sore from friction) ላጠ

rub out ሰረዘ

rubber ላስቲክ ; (eraser) ላጲስ ; (rubber shoes) የጎማ፡ ጫማ

rubber band ላስቲክ

rubber stamp ማኅተም

rubbish ጥራጊ

rubble ፍርስራሽ

turn to rubble አመድ፡ አደረገ

rudder መቅዘፊያ

rude (not polite) ባለጌ ; (roughly made) እንደነገሩ፡ ← የተሠራ

rudeness ብልግና

rudiments መሠረታዊ፡ ደንቦች

rudimentary መጠነኛ

rue አዘነ

ruffian ወሮበላ

rug ስጋጃ

rugged (countryside) ወጣ፡ ገባ፡ (people) ጠንካራ ; (weather) አስቸጋሪ

ruin, (v.) አጠፋ; (health) ጎዳ ; (clothes, road) አበላሸ ; (make bankrupt) አከሰረ

ruin (n.) ጉዳት፤ ጥፋት

ruins ፍራሽ

be in ruins ፈረሰ

ruinous ጥፋት፡ የሚያደርስ

rule, v. (govern) ገዛ ; (exercise authority) አስተዳደረ ; (make a formal decision) ፈረደ; (make straight lines) አሠመረ; (restrain) ገታ

rule (n.) ሕግ፤ ደንብ ; (government) አገዛዝ ; (the usual thing) የተለመደ

as a rule ዘወትር

ruler (who governs) ገዢ ; (for making lines) ማሥመሪያ

ruling, n. (of court) ውሳኔ

ruling, adj. (classes) የገዢዎች ; (party) በሥልጣን፡ ላይ፡ ያለ; (factor) ዋና

run, vt. (administer) አስተዳደረ፤ ← አካሄደ ; (enter into a race) አስገባ ; (a candidate)

←አቋረጠ ; (water) ሰቀቀ; 2 (make a car collide) አጋጨ; 2 (a cable) ዘረጋ ; (publish a story) አወጣ

run (vi.) ሮጠ ; (of train) ሄደ ; (of bus) ተመላለሰ ; (of river) ገባ ; (of road) አለፈ ; (of machine, watch) ሠራ ; (of stockings) ተዘረዘረ ; (of color) ለቀቀ ; (be shown) ታየ ; (compete) ተወዳደረ

run about ወዲያ፡ ወዲህ፡ ሮጠ

run across አጋጠመ

run along ሄደ

run away ሸሸ

run into (collide) ገጨ

run out ሮጦ፡ ወጣ ; (come to an end) አለቀ

run (n.), in the --- long የኋላ ←ኋላ

runner (who runs) ሯጭ ; (long thin rug) ቀጭን፡ ምንጣፍ

running (n.) ሩጫ ; (administering) አስተዳደር

be in the running ተወዳዳሪ፡ ነው

running water የሚፈስ፡ ውኃ

rural የገጠር

ruse ዘዴ

rush, vt. (cause to act fast) ←አጣደፈ ; (a job) አቻኰለ ; (send fast) በፍጥነት፡ ላከ; (bring fast) በፍጥነት፡ ወሰደ; (attack swiftly) ድንገት፡ አጠቃ

rush (vi.) ቸኰለ

rush out ተንጋግቶ፡ ወጣ

rush, n. (hurry) ጥድፊያ ፤ የሚደርስ ችኰላ፡ ነገር

(state of unusual activity) ←ግርግር ፤ ጋጋታ ; (marsh plant) ሙፋ

be in a rush ቸኰለ

Russia ሩሲያ ፤ ሙስኮብ

Russian (member of Russia) ሙስኮብ ; (language) ሙስኮብኛ

rust (v.) ዛገ

rust (n.) ዝገት

rustic (furniture) ያገር፡ ቤት ; (manners) የባላገርነት

rustle (skirt) ተንሿሿ ; (leaves) ተንኰሸኰሸ

rusty የዛገ

ruthless, be --- ጨከነ

ruthlessly በጭካኔ ፤ ያለ፡ ምሕረት

rye አጃ

S

Sabbath ሰንበት፤ ቅዳሜ

sack ጆንያ

sacred የተቀደሰ ; (memory of a hero) የጀበረ

sacrifice (v.) ሠዋ፤ መሥዋዕት፡ አቀረበ

sacrifice oneself ራሱን፡ ← መሥዋዕት፡ አደረገ

sacrifice (n.) መሥዋዕት

sacrilege የረከሰ፡ ተግባር፤ ዐግሬከት

sad አሳዛኝ

be sad አዘነ

feel sad ሐዘን፡ ተሰማ

sadden አሳዘነ

saddle (v.) ጫነ

saddle (n.) ኮርቻ

sadness ሐዘን

safe (n.) ካዝና

safe (adj.) ደኅና ; (driver) ጥንቁቅ ; (reliable) የሚያስተማምን ; (peaceful) ሰላም

be safe ደኅና፡ ነው

feel safe ስጋት፡ አላደረበትም

safely በደኅና

safety ደኅንነት ; (safe place) ካደጋ፡ የሚድንበት፡ ስፍራ

sagacious ብልህ

sage ዐዋቂ፡ ሊቅ

sail (n.) የመርከብ፡ ሸራ

sailor መርከበኛ

saint ቅዱስ

sake, for the --- of ለ---ሲል፤ ← ለ . . . ብሎ

salad ሰላጣ

salary ደሞዝ

sale መሸጥ ; (selling at a lower price than usual) የምግሬያ ← ሽያጭ፡ ጊዜ

sales clerk አሻሻጭ

salesman አሻሻጭ፤ ሻጭ

saliva ለሀጭ፤ ምራቅ፡

salt (v.) ጨው፡ ጨመረ

salt (n.) ጨው

salty, be --- ጨው፡ በዛበት

salutary ለጤና፡ ጥሩ፤ ለጤንነት፡ የሚስማማ

salutation ሰላምታ

salute (v.) ሰላምታ፡ ሰጠ

salute (n.) ሰላምታ

salvation ደኅንነት

salve ቅባት ; (something soothing, words) ማጽናኛ

same, the --- ያው፤ አንድ

sample (n.) ናሙና፤ ለሙና

sanctify (consecrate) ባረከ ; (cause to be considered ~~ቅዱስ~~: ~~አደረገ~~

sacred) ቅዱስ፡ አደረገ

sanction (v.) ፈቀደ

sanction (n.) ፈቃድ

sanctuary መቅደስ ; (refuge and protection) ጥገኝነት

sand (n.) አሸዋ

sandal የነጠላ፡ ጫማ

sandy አሸዋማ

sane ጤነኛ

sanitary (free from disease) ንጹሕ; (having to do with health) ← የጤና፡ አጠባበቅ

sanity አእምሮ

sapphire ዕንቍ፡ ሰንፔር

Satan ሰይጣን

satiable, be --- ረካ

satiate አጠገበ

satiety ጥጋብ

satin አጥላስ

satisfaction ደስታ

satisfactory (condition) ደኅና; (reason) በቂ ; (results) አጥጋቢ

satisfy (of content) አስደሰተ : (of an answer) አጠገበ፤ አሳረደ (~~the~~ hunger) አስታገሠ ፤ ረካ

Saturday ቅዳሜ

sauce ስጎ

savage (n.) አረመኔ ፤ ያልሠለጠነ፡ ሰው

savage, adj. (~~of an~~ attack) ኃይለኛ; (~~of a~~ lion) ቁጡ ; (~~of~~ outlaw~~s~~) ጨካኝ ፤ አረመኔ

save አዳነ ; (money) አስቀመጠ፤ ቆጠበ (a seat) ያዘ

savings ያጠራቀመ፤ ተቀማጭ፡ ገንዘብ

Savior መድኃኒታችን

savor (n.) ጣዕም

savory, be --- ጣፈጠ

saw (v.) በመጋዝ፡ ቈረጠ፤ መጋዝ

saw (n.) መጋዝ

say አለ

that is to say ማለት

saying ምሳሌ

scab ቅርፊት

scald (burn) አቃጠለ ; (milk) ← አፈላ

scale, n. (scrape off) ፋቀ ; (climb) ወጣ

scale (of fish) ቅርፊት ; (graduated marking) መስፈሪያ; (hierarchy) ደረጃ

scales ሚዛን

scalp (n.) አናት

scan (look through hastily) በችኰላ፡ መልከት፡ መልከት፡ አደረገ

scandal አሳፋሪ፡ ነገር፤ ነውር

scanty ጎደሎ ; (costume) በጣም፡ አጭር

scar (n.) ጠባሳ

scarce ብርቅ

be scarce ጠፋ፤ የለም

scarcely እምብዛም + negative verb

scarcity እጥረት

scare (vt.) አስደነገጠ

be scared ፈራ

scarf ያንገት፡ ሸማ

scary የሚያስፈራ

scatter (vt.) በታተነ፤ በተነ

scatter (vi.) ተበታተነ

scene (place of action) ስፍራ፤ ቦታ; (incident) ሁኔታ ; (division of an act) ትዕይንት ; (setting of a play) የቲያትር፡ ትርእይት

scenery (general view) ትርእይት ; (of a stage) የቲያትር፡ ትርእይት

scenic ውብ

scent (of flowers) መዓዛ ; (perfume) ሽቶ ; (sense of smell) የማሽተት፡ ችሎታ

schedule (of prices) ዝርዝር ; (of plane) መነሻ፡ መድረሻ ← የሚገልጽ፡ ፕሮግራም

scheme (v.) ዶለተ

scheme, n. (plan, design) ዘዴ፤ እቅድ ; (plot) ሴራ ; (arrangement, layout) ድልድል

scholar ሊቅ

scholarly የምሁር፡

scholarship (quality of learning) ሊቅነት ; (grant) የነፃ፡ ትምህርት፡ ዕድል

school ትምህርት፡ ቤት

send to school አስተማረ

schooling ትምህርት

science ሥነ፡ ፍጥረት

scientist የሣይንስ፡ ሊቅ

scintillate አንጸባረቀ

scissors መቀስ

scold ገሠጸ፤ ወቀሰ

scorch አቃጠለ

be scorched አረረ

score, v. (a goal) አገባ ; (keep account) ቈጠረ

score, n. (in a game) ነጥብ ; (result) ውጤት ; (of music) ሰሌዳ ; (set of twenty) ሃያ

scores of ብዙ

keep score ቈጠረ

scorn (v.) አንቋሸሸ

scorn (n.) ንቀት

scornful የንቀት

scorpion ጊንጥ

scoundrel ወሮበላ

scour (a pot) ፈቀፈቀ ; (floor) ፋቀ ; (search thoroughly) አሰሰ

scourge (n.) መቅሠፍት

scout (v.) ቃኘ

scout, n. (person sent out to get information) አሳሽ ; (boy scout) እስካውት

scramble (v.) ተሻማ

scramble (n.) ሽሚያ

scrap, n. (of paper) ብጣሽ ; (of meat) ቁራጭ ; (junk) ቁርጥራጭ

scraps ፍርፋሪ

scrape (v.) ፋቀ ; (the skin) ላጠ

scrape along እንደምንም፡ ኖረ

scrape off ፋቀ

scratch, vt. (paint) ፋቀ ; (the skin) ቧጠጠ ፤ ቧጠረ ; (a match) ጫረ

scratch, vi. (relieve itching by scraping the skin) አከከ ; (of pen) ጫረ

scratch out ሰረዘ

scream (v.) ጮኸ

scream (n.) ጩኸት

screech ሲጢጥ፡ አለ

screen, v. (hide with) ከለከለ ፤ ጋረደ; (candidate) መረጠ

screen (n.) የሽቦ፡ ወንፊት

(motion picture) ፊልም

screw (n.) የቆርንጊጭ፡ ምስማር

screwdriver የጠመንጃ፡ መፍቻ

scribe ቁም፡ ጸሐፊ

script ፊደል

Scriptures መጽሐፍ፡ ቅዱስ

scrub ጠረገ ፤ ፈተገ

scrutinize በጥንቃቄ፡ መረመረ

scuffle (v.) ታገለ

sculptor ቅርጽ፡ አውጪ ፤ ሐውልት፡ ሠሪ

sculpture ቅርጽ

scum (of milk) ስልባቦት ; (of water) ቆሻሻ ; (worthless people) ልክስክስ፡ ሰዎች

scythe ማጭድ

sea ባሕር

seal, v. (enclose tightly) አሸገ ; (affix a seal to a document) ማኅተም፡ አኖረ

seal (n.) ማኅተም

seam (v.) ሰፋ

seam (n.) ስፌት ፤ ዘርፍ ; (a line where edges join) መጋጠሚያ

seaman መርከበኛ

seamstress ልብስ፡ሰፊ

search (v.) ፈተሸ፤ በረበረ

search (n.) ፍተሻ፤ ፍለጋ

searchlight ባውዛ

seashore የባሕር፡ዳርቻ

season (v.) አጣፈጠ

season (n.) ወቅት

seasoning ቅመም

seat (v.) አስቀመጠ;
(have seats for) ያዘ

seat (n.) ወንበር፤ መቀመጫ;
(for a play) ቦታ ; (place where anything is located)
← ስፍራ

have a seat, take a seat
← ተቀመጥ

seclude ጋረደ

secluded (life) የብቸኝነት ;
(place) ፈንጠር፡ ያለ፤ ገለልተኛ

seclusion ገለልተኝነት

second (v.) ደገፈ

second (n.) ሰከንድ

in just a second አሁኑኑ

second (adj.) ሁለተኛ ; (of prize)
ባሁለተኛነት

Second (connected with a king)
← ዳግማዊ

secondary school ሁለተኛ፡ ደረጃ፡ ትምህርት፡ ቤት

second-hand (book) አሮጌ ; (car)
ያገለገለ

secret (n.) ምስጢር

secret (adj.) የምስጢር፤ የተሰወረ

secretariat ጽሕፈት፡ ቤት

secretary ጸሐፊ

secretary general ዋና፡ ጸሐፊ

secretly በድብቅ

sect ወገን

section (n.) ክፍል ; (of orange)
ፍልቃቂ ; (of town) ሰፈር

secular (music) ዓለማዊ ; (court)
የሕዝብ ; (education) ሥጋዊ

secure, v. (tie) በደንብ፡ያዘ ;
(protect) ተከላከለ ; (obtain a seat) ያዘ ; (ensure) ~~[illegible]~~
አስከበረ ; (guarantee)
← በዋስትና፡ጠበቀ

secure, adj. (life) ሰላማዊ ;
(hiding place) የማያሰጋ ;
(foundation) ጽኑ ; (investment) ኪሳራ፡የማያደርስ

keep secure ጠበቀ

security (pledge) መያዣ ;
(protection) መከላከያ;
(means of safety) ዋበቃ

Security Council የጸጥታ፡ ምክር፡ ቤት

sedentary (tribe) ሰፋሪ፡ የማይዞር;
(accustomed to much sitting)
← መቀመጥ፡ የሚያበዛ፡

sediment ደለል

seduce አባበለ

see አየ : (escort) ሸኘ ;
(visit) ጠየቀ ; (understand)
← ገባ(ው)

seed (v.) ዘራ

seed (n.) ዘር

seedling ችግኝ

seek ፈለገ ; (appeal for) ጠየቀ ;
(try) ሞከረ

seem መሰለ

seesaw, v. (ride a seesaw)
ሚዛን፡ ተጫወተ; (hesitate)
አወላወለ

seesaw (n.) ሚዛን

segment ክፋይ

segregate (a prisoner) ለብቻ፡ አደረገ
(a sick person) ገለልተኛ፡ቦታ፡ አስተኛ

seize ያዘ ; (grasp with the
mind) ተረዳ

seldom እምብዛም + negative verb;
ብዙ፡ ጊዜ + negative verb

select (v.) መረጠ

select (adj.) የተመረጠ፤ ምርጥ

selection ምርጫ

self-confidence በራስ፡ ላይ፡ ያለው፡ እምነት

selfish ራሱን፡ ወዳድ፤ ለራሱ፡ ብቻ፡ የሚል

sell ሸጠ

semester የትምህርት፡ ዘመን፡ አጋማሽ

semicolon ነጠላ፡ ሰረዝ

Semite ሴማዊ

senate የሕግ፡ መወሰኛ፡ ምክር፡ ቤት

send ላከ ; (regards) አቀረበ
send back መልሶ፡ ላከ
send forth ላከ
send in አስገባ

senior (adj.) የበላይነት፡ ያለው

seniority ያገልግሎት፡ ዘመን

sensation ስሜት

sensational ስሜት፡ የሚቀሰቅስ

sense, v. (feel) ተሰማ(ው);
(understand) ተረዳ(ው)

sense, n. (sensation) ስሜት;
(power of the mind to know
what happens outside itself),
ሕዋስ ; (meaning) ትርጉም
common sense የተፈጥሮ፡ ዕውቀት
make sense of something ገባ(ው)
be out of one's senses አእምሮውን ሳተ

senseless (foolish) የማይረባ ;
(unconscious) ነፍሱን፡ ሳተ

sensible (person) አስተዋይ;

(advice) ጠቃሚ ; (clothing) ←የሚስማማ

sensitive, be --- to ተሰማ(ው)

sentence (v.) ፈረደ(በት)

sentence, n. (in grammar) ዓረፍተ፡ ነገር ; (of court) ፍርድ

death sentence የሞት፡ ፍርድ

sentiment (feeling) ስሜት ; (belief) አስተያየት

sentinel ዘብ

separate (vt.) ነጠለ ; (fighting persons) ገላገለ

separate (vi.) ተለየ

separate (adj.) የተለየ

separately ለየብቻ

separation መለየት፤ መለያየት

September መስከረም

sepulchre መቃብር

serene (sky) የጠራው ; (sea) ጸጥ፡ ያለ

serf ገባር

sergeant የሃምሳ፡ አለቃ

series ተራ

serious (person) ኮስታራ፤ ←ምራቁን፡ የዋጠ፡ ሰው

(situation) አሳሳቢ፤ ከባድ ; (mistake) ከባድ ; (difficulties) ከፋ፡ ያለ ; (book) ←ጠለቅ፡ ያለ

seriously (ill) በጠና ; (in earnest) ከልብ

seriousness (of situation) አሳሳቢነት ; (of crime) ከባድነት

sermon ስብከት

serpent እባብ

servant አሽከር

serve (vt.) አገለገለ ; (food) ←አቀረበ

be served (food) ቀረበ

service (n.) አገልግሎት ; (religious ceremony) ቅዳሴ; (set of dishes) እቃዎች

services እርዳታ

be of service ረዳ

render service አገለገለ

service station የቤንዚን፡ ማደያ

servitude ባርነት

session ስብሰባ ; (of court) ችሎት

set, vt. (place) አስቀመጠ ; (the time) ወሰነ ; (decorate) አጌጠ ; (a broken arm) ጠገነ ; (a clock) እንዲደውል፡ ሞላ

(regulate) አስተካከለ

set, vi. (of sun) ጠለቀ

set apart (put aside) አስቀመጠ ; (distinguish) ለየ

set aside አስቀመጠ

set down አወረደ

set up አቆመ

settle, vt. (an argument) ← አቆመ፤ መልስ; (affairs) ← አጠናቀቀ; (a business) ← ፈጸመ ; (bills) ከፈለ

settle, vi. (make one's home) ← ተቀመጠ; (come to an agreement) ተስማማ ; (of coffee) ሰከነ

settle down ቋሚ፡ ኾነ

settlement (colony) ቅኝ፡ ግዛት; (dwelling) መኖሪያ ; (agreement) መስማማት

settler ሰፋሪ

seven ሰባት

seven o'clock አንድ፡ ሰዓት

seventeen ዐሥራ፡ ሰባት

seventh ሰባተኛ

seventy ሰባ

sever ቈረጠ ; (relations) አቋረጠ

several (pron.) እንዳንዶች

several (adj.) በርካታ፡ ያሉ፤ ብዙዎች

severe ኀይለኛ ; (strict) ~~ጠባቂ~~ ጥብቅ ; (pain) አሳማሚ; (sentence) ጽኑ ; (competition) ገዴ፡ ልክ ; (dress) ጌጥ፡ ጌጥ፡ የሌለበት

sew ሰፋ

sewage ቆሻሻ፡ ፍሳሽ፤ የቆሻሻ፡ ፍሳሽ

sewer ቱቦ

sewing ስፌት

sewing machine የስፌት፡ መኪና

sex ጾታ

shabby (beggar) ሰጎታም; (clothes) ያለቀ

shack ጎጆ

shackle (n.) እግር፡ ብረት

shade, vt. (throw shade) አጠላ; (protect from glare) ከለለ

shade (n.) ጥላ ; (of a window) ← የሸሌ፡ መጋረጃ

shadow (v.) ጥላ፡ ጣለ(በት) ; (keep under observation) ነፍቃበት. ← ተከታተለ

shadow (n.) ጥላ

shake (vt.) አንቀጠቀጠ; (of wind) ← አወዛወዘ ; (the rug) አራገፈ ; (the head) ነቀነቀ ; (the hand) ጨበጠ

shake (vi.) ተንቀጠቀጠ; (of

voice) ቁርጥ፡ ቁርጥ፡ አለ

shake hands ተጨባበጠ

shaky (bridge) የሚያረገርግ

(excuse) የማይረባ

shallow ገልብ፤ ጥልቅ፡ ያልሆነ፤ ቁርብ

(dish) ዝርግ

shambles, be --- ተመሰቃቀለ

shame (n.) ኀፍረት

bring shame to አሳፈረ፤ አዋረደ

put to shame ቅጌ፡ አሳጣ፤ አሸማቀቀ

what a shame! ያሳዝናል

shameful አሳፋሪ

shape, v. (give form to) ቅርጽ፡ አበጀለት ; (adjust) አዛመደ

shape (n.) ቅርጽ ; (appearance) ተመስሎ ; (condition) ሁኔታ፤ መልክ

share (vt.) ተካፈለ፤ ተከፋፈለ

share (vi.) ድርሻውን፡ ሠራ፤ አዋጣ

share (n.) ድርሻ ; (parts into which the ownership of a company is divided) አክሲዮን

sharp (pencil) ሹል፤ የሾለ ; (knife) ስል፤ ስለታም ; (pain) ኀይለኛ ; (curve) ድንገተኛ; (contrast) ጉልህ

sharp, adv. (on time) ልክ

sharpen (a knife) ሳለ ; (a pencil) ቀረጸ

shatter ሰባበረ፤ ስንጥቅጥቁን፡ አወጣ

shave (vt.) ላጨ

shave (vi.) ተላጨ

shaver ጢም፡ መላጫ

shawl ያንገት፡ ልብስ

she እሷ፤ እርሷ

shear (v.) ሸለተ

shears ትልቅ፡ መቀስ

sheath (of sword) አፎት ; (covering) ሽፋን

shed, v. (skin) ገፈፈ; (blood) አፈሰሰ; (clothes) አወለቀ

shed (n.) መጠለያ

sheep በግ

sheer (stockings) ስስ ; (madness) ፍጹም

sheet አንሶላ

shelf መደርደሪያ ; (of rack) እርከን

shell, v. (beans) ፈለፈለ ; (eggs) ላጠ ; (bombard) በመድፍ፡ ደበደበ

